# አዲስ ዘመን

እፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 101 ታኅሣሥ 11 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ለሀገር ውስጥ ባንኮች ዕድል ወይስ ስጋት?




**ሞገስ ተስፋ**

**ዜና ትንታኔ**

በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ከተጀመረ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ እድሜ አለው። በእነዚህ ጊዜያትም ያጋጠሙትን መልካም እድሎች እና ፈተናዎች ተሻግሮ ዛሬ ላይ ደርሷል። የዛሬ ቁመናውም ቢሆን የእድሜውን ያህል እንዳልሆነ በዘርፉ የተሠማሩ ምሁራን ይናገራሉ።

ይህንን እውነታ ለመለወጥ መንግሥት የባንኩን ዘርፍ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ማድረግ የሚያስችል አዋጅ አርቅቆ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅርቡ እንዲጸድቅ አድርጓል። የሕጉ መጽደቅ በብዙ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ አሁንም ዜጎችም ሆነ በመስኩ የሚገኙ ምሁራን የመነጋገሪያ አጀንዳ እንደሆነ ነው።

የውጭ ባለሀብቶች በባንክ ዘርፍ እንዲሠማሩ የሚፈቅደው አዋጅ ለሀገር ውስጥ ባንኮች ምን ይዞ ይመጣል፤ ተስፋ ወይስ ስጋት? በሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው ጠቀሜታስ ምን ይመስላል በሚለው ሃሳብ ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

አቶ ክቡር ገና ይባላሉ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ናቸው። አዋጁ መጽደቁ የውጭ ባንኮች ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲሠሩ የሚጋብዝ መሆኑን፤


የውጭ ባንኮች... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# ለአትሌቲክሱ ማን ምን ሊሠራ አቀደ?

**ብርሃን ፈይሳ**

**ዜና ሐተታ**

አትሌቲክስ የኢትዮጵያ ኩራትና መገለጫ ነው። የኢትዮጵያውያን አልሸነፍ ባይነትና ወኔ በዓለም አደባባይ የሚገለጥበት፣ እልፍ ጀግኖች ለሰንደቅ ዓላማ ክብር የሚዋደቁበት በመሆኑም ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከስፖርትም የዘለለ ትርጉም አለው። ስፖርቱ በዚህ ደረጃ ዋጋ እንዲሰጠውም ብርቅዬ አትሌቶች ለዘመናት ድል ችቦ እየተቀባበሉ አሁን ድረስ ዘልቀዋል።

ያም ሆኖ ስፖርቱ በየጊዜው የሚገጥሙት አስተዳደራዊ እንቅፋቶች ሀገርን በታላላቅ ዓለም አቀፍ መድረኮች ውጤት እንዲቀዛቀዝ ከማድረጉ በተጨማሪ ስፖርቱ ወደ ባሰ ችግር ሲያመራ ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት ታዝበናል። ስፖርቱ በብዙ አስተዳደራዊ


ለአትሌቲክሱ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል




ዶክተር ሳዲቅ ታጁ

## የጨቅላ ሕፃናት የዓይን በሽታ እልባት ካልተሰጠው በሀገሪቱ የዓይነ ስውራን ቁጥር ይጨምራል

- በሁለት ሆስፒታሎች ህክምና ካገኙ ህፃናት መካከል 48 በመቶ የችግሩ ሰለባ ናቸው


6


# በኦሮሚያ ክልል ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል የአቮካዶ ምርት ተሰበሰበ

## - 165 ሺህ 321 አርሶ አደሮች በአቮካዶ ልማት ተሠማርተዋል

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- በ2017 የምርት ዘመን ሰባት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እስካሁን ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል የአቮካዶ ምርት መሰብሰቡን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ። በክልሉ 165 ሺህ 321 አርሶ አደሮች በአቮካዶ ልማት መሠማራታቸው ተጠቁሟል፡፡

በቢሮው የፍራፍሬ ልማት ዳይሬክተር አቶ ተገኝ ኢራና ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በክልሉ የአቮካዶ ማሳ ሽፋን 55 ሺህ 112 ሄክታር መሬት የደረሰ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 30 ሺህ 145 ሄክታር የሚሆነው መሬት ላይ የተተከለው የአቮካዶ ዛፍ ምርት እየሰጠ ይገኛል፡፡

ባለፈው ዓመት ስድስት ነጥብ አምስት ኩንታል የአቮካዶ ምርት ማግኘት መቻሉን አውስተው፤ በዘንድሮው የምርት ዘመን ሰባት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እስካሁንም ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል የአቮካዶ ምርት መሰብሰቡን ተናግረዋል፡፡

በክልሉ በ21 ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 185 ወረዳዎች በአንድ ሺህ 751 ክላስተር በማደራጀት አቮካዶ መተከሉን የገለጹት አቶ ተገኝ፤ 165 ሺህ 321 ወንድና ሴት አርሶ አደሮች በአቮካዶ ማልማት ሥራ ተሠማርተው እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡ በዚህም ተጠቃሚ እየሆኑ እንደመጡ ጠቁመዋል፡፡

ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ በዘንድሮው ዓመት ወደ ጎረቤት ሀገራት እና መካከለኛው ምስራቅ የአቫካዶ ምርትን መላክ ተችሏል፡፡ ወደ አውሮፓ አንድ ሺህ ኩንታል የአቮካዶ ምርት ለመላክ ታቅዶ ከዚህም መካከል 610 ኩንታል ምርት ኤክስፖርት ተደርጓል።


በኦሮሚያ ክልል... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





ዜና



ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ

## ከተሞቹ ምርትን መደበቅና ያለደረሰኝ ግብይትን ለመከላከል በጋራ እየሠሩ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ እና ሸገር ከተሞች ምርትን መደበቅ፣ ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወንና መሰል ወንጀሎችን ለመከላከል በጋራ እየሠሩ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ገለጸ፡፡ በአዲስ አበባ እና በሸገር ከተሞች የሚፈፀም የኢኮኖሚ አሻጥር ወንጀልን በቅንጅት ለመከላከል የስምምነት ፊርማ ትናንት ተፈራርመዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ በስምምነቱ ወቅት እንደተናገሩት፣ በአዲስ አበባና በሸገር ከተሞች የሚፈፀሙ የኢኮኖሚ አሻጥር ወንጀሎችን ማለትም ምርትን መደበቅ፣ ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን፣ ባዕድ ነገሮችን ቀላቅሎ ለገበያ ማቅረብና መሰል ወንጀሎችን ለመከላከል የፀጥታ አካላት በጋራ እየሠሩ ነው፡፡ ስምምነቱም የኢኮኖሚ አሻጥር ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ እና የሸገር ከተማ የሰላምና የፀጥታ ቢሮዎች እየሠሩት ባለው ሰላምና ፀጥታን የማስከበር ሥራ በኢኮኖሚው ዘርፍ ላይ የሚፈፀሙ የአሻጥር ወንጀሎችን ምጣኔም መቀነስ መቻሉን አመልክተው፣ እየተሠራ ያለው ቅንጅታዊ ሥራ ቅርፃቸውንና ይዘታቸውን እየቀያየሩ ለሚፈፀሙ የኢኮኖሚ ወንጀሎችን ለመከላከል እያስቻለ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ስምምነቱም ቅንጅታዊ አሠራሩን ይበልጥ በማጠናከር ከአዲስ አበባ ወደ ሸገር፣ ከሸገር ወደ አዲስ አበባ ከተማ እየተዘዋወሩ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል መሆኑ ተናግረዋል፡፡

በሁለቱ ከተማዎች እየተሠሩ ያሉ ሰላምና ፀጥታን የማስከበር ሥራ የአዳባባይ በዓላትና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲካሄዱ አስችሏል ያሉት የቢሮ ኃላፊዋ፣ መዲናዋ ትልልቅ ኢኮኖሚዎች የሚንቀሳቀሱባት፣ ዲፕሎማቶች የሚኖሩባትና የቱሪስት ፍስት ያለባት ከተማ እንደመሆኗ ይህን የሚመጥን ሰላምና ፀጥታ የማስከበር ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ወንጀሎችን ከምንጫቸው ለማድረቅም በሁለቱ ከተማዎች ሕዝብን ከሕዝብ የማገናኘትና የሰላም ባለቤት የማድረግ ሥራ ይሠራል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ሕዝብን የሰላም ባለቤት በማድረግ፣ ከሸገር ከተማ አስተዳደር የፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የመዲናዋን ሰላምና ደህንነት የማስከበር ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሸገር ከተማ ምክትል ከንቲባ የኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪ አቶ ጉዮ ገልገሎ በበኩላቸው፣ ስምምነቱ የኢኮኖሚ አሻጥር ወንጀሎችን በቅንጅት ለመከላከል ትልቅ ሚና አለው ብለዋል።

በሁለቱ ከተሞች በቅንጅት እየተሠራ ያለው ሰላምና ፀጥታን የማስከበር ሥራ የአደባባይ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ማድረግ አስችሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የንግድ እንቅስቃሴን፣ የኢኮኖሚ እድገትን ለማሳለጥና ዜጎች ምቹ ሕይወት እንዲኖሩ ሰላም አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ጉዮ፣ የሀገርን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማስቀጠልና የዜጎችን በሰላም ወጥቶ በሰላም የመግባት ዋስትናን ለማረጋገጥ እየሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል፡፡

# ላኪዎች በቀጣይ ጠንካራ ውድድር እንደሚጠብቃቸው ተረድተው መዘጋጀት እንዳለባቸው ተጠቆመ

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ላኪዎች በቀጣይ ጠንካራ ውድድር እንደሚጠብቃቸው ተረድተው እራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው የጥራጥሬና ቅባት እህሎች ላኪ ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ኤዳኦ አብዲ አሳሰቡ። በጥራጥሬና ቅባት እህሎች ዙሪያ የተደረገ ጥናት ላይ ውይይት ተካሄደ፡፡

አቶ ኤዳኦ አብዲ በጥራጥሬና ቅባት እህሎች ላኪዎች እና የምርት ሂደት ላይ እያጋጠሙ ስላሉ ማነቆዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ውይይት እንደገለጹት፣ በውጭ ንግድ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ባለሀብቶች/ላኪዎች ተወዳዳሪ ለመሆን እራሳቸውን በሰው ሃይልና በቴክኖሎጂ በማብቃት የሚልኩት ምርቶች ላይ እሴት ሊጨምሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ከውጭ የሚገቡ ባለሀብቶች በቂ የሆነ የፋይናንስ፣ የመዳረሻ ቦታ፣ የመረጃ እና የሰው ሃይል ያላቸው ስለሆኑ ለኢትዮጵያ ላኪዎች መረጃን ከማዳረስ አኳያ በጎ ሚና ይኖራቸዋል ያሉት አቶ ኤዳኦ፣ ኢትዮጵያውያኑ ባለሀብቶች በእነሱ ልክ የገበያ መዳረሻ እና የሽያጭ አቅም እንደሌላቸው አመልክተዋል።

የወጪ ንግድ የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ መሆኑን ጠቁመው፣ ማህበሩም ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር እና የውጭ ንግዱ እንዲሳለጥ ከጂ አይ ዜድ ጋር በመተባበር ጥናት ማስጠናቱን አስታውቀዋል፡፡



አቶ ኤዳኦ አብዲ

ጥናቱ ከፋይናንስ፣ ከሎጂስቲክስ፣ ከፖሊሲ፣ ከገበያ እና ከንግድ ትስስር አንጻር በሀገሪቱ ያሉ አስቻይ ሁኔታዎች እና ማነቆዎች በዝርዝር ማስቀመጡን አመልክተው፣ የውይይቱም ዓላማም ባለድርሻ አካላት በጥናት በተደገፉ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረው ችግሮችን ለመቅረፍ በጋራ እንዲሠሩ ለማድረግ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በጥናቱ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር ፣ የላኪዎቹ ሚና እና በአጠቃላይ ዘርፉ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማት ምን ማድረግ አለባቸው የሚለውን በዝርዝር የተመለከተ ስለመሆኑም አብራርተዋል፡፡

ጥናቱን ያቀረቡት የኢንቨስት ኮንሰልት ጀነራል ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ተመስገን ተስፉ በበኩላቸው፣ በጥናቱ ለዘርፉ ማነቆ ናቸው ተብለው የተለዩት ጉዳዮች ከፖሊሲና ከሕግ ጋር የተያያዙ፣ ከፖሊሲ ውጭ በመንግሥት ሴክተር የሚስተዋሉ እና አተገባበር (ኦፕሬሽናል) የሆኑ ተብለው በሶስት የተከፈሉ ናቸው፡፡

ጥናቱ የተሠራው ከጥራጥሬና ቅባት እህሎች ላኪ ማህበር አባላት እና ከሌሎች የባለድርሻ አካላት ከተሰበሰቡ መረጃዎች መሆኑን ገልጸው፣ ጥናቱ አሁን ገበያው ላይ ለሚሳተፉ እና አዳዲስ ለሚመጡ ነጋዴዎች ንግዱ ላይ ያለውን ከባቢያዊ ሁኔታ በግልጽ የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በውይይቱም ከተሳታፊ ባለድርሻ አካላት ከተነሱ ችግሮች መካከል ፣ ለላኪዎች ብቁ የሆነ እገዛ ከሴክተር መሥሪያ ቤቶች አለማግኘት፣ በጥራጥሬና ቅባት እህሎች ለማምረት መሬት ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ መርዘም፣ በፋይናንስ ተቋማት የገንዘብ አቅርቦት እጥረት ፣ የጸጥታ ችግር ባሉባቸው አካባቢዎች የሚጠየቀው የትራንስፖርት ክፍያ ከፍተኛ መሆን እና ልውጠ ህያዋን (ጂኤምኦ ሰርተፍኬት) ለማግኘት ያለው ሂደት በዋንኛነት ተጠቃሽ መሆናቸው ተመልክቷል፡፡

# የመገናኛ ብዙሃን ሚና በሀገራዊ ምክክሩ

**ነፃነት አለሙ**

**ዜና ሀተታ**

ከተቋቋመ ሶስተኛ ዓመቱን ሊያስቆጥር ሁለት ወራቶች የቀሩት ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እስካሁን በነበረው ቆይታ ምክክሩን ለመጀመር መጠነ ሰፊ ሥራዎችን እየሠራ ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያትም የተለያዩ ሂደቶችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ሂደቶች አንስቶ እስከ ምክክሩ መጠናቀቂያ ድረስ የመገናኛ ብዙሃን ሚና ምን መሆን አለበት በሚለው ዙሪያ የመገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ከዩኤንዲፒ ጋር በመተባበር የውይይት መድረክ አዘጋጅቷል፡፡

በውይይት መድረኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አብዲሳ ዘርአይ (ዶ/ር) በበኩላቸው በምክክር ሂደቱ ለመገናኛ ብዙሃን ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ያነሳሉ፡፡

መገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ፅንፎች የመወሰድ፣ የተለያዩ አካላት ፍላጎት ማንፀባረቂያ መሆን፣ የባለሙያዎቻቸውን ደህንነት አለመጠበቅ እንዲሁም የባለሙያዎቻቸው ልምድ ማነስ በተለይም ሀገራዊ ምክክር እንዴት እንደሚዘገብ አለማወቅ ተግዳሮቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፡፡

መገናኛ ብዙሃን እንደተቋም የራሳቸውን አጀንዳ ማስያዝ እንዳለባቸው የጠቆሙት መምህሩ፣ ሀገራዊ የምክክር ሂደቱን ከተጠቀሙበት አዎንታዊ ሚና የመጫወት እድል እንዳላቸው ይጠቁማሉ፡፡ በሂደቱም መገናኛ ብዙሃን ማህበረሰባዊ መተማመንን የሚሸረሽሩ ቁስሎችን የማሻር ሚና እንደሚኖራቸው ነው የገለጹት፡፡ ይህም ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት ጉልህ ሚና የሚጫወቱበትን ዕድል ይፈጥራል ነው ያሉት፡፡

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ወንድሙ ለገሰ (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ የመገናኛ ብዙሃን ዋነኛ ሥራ ማስተማር፣ ማዝናናትና መረጃ መስጠት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ መገናኛ ብዙሃኑ ማህበረሰቡን ወደ አንድ ለማምጣትና አካታች ለማድረግ ሲነሱ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ መሥራት አለባቸው፡፡

የመጀመሪያው የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ታሪክ ላይ መሥራት ነው የሚሉት መምህሩ፣ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚ ላይም ማህበረሰቡን እኩል ተሳታፊ ባደረገ መልኩ መሥራት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር መገናኛ ብዙሃን ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ መሆን እንደሚገባቸውም ያነሳሉ፡፡በተጨማሪም የዘር፣ ሃይማኖትና የጾታ ጉዳዮች ላይ አድሎአዊ ባልሆነ መልኩ መሥራት እንዳለባቸው የጠቆሙት መምህሩ፣ ሚዲያው ሁሉንም ማህበረሰብ አንድ የሚያደርግ ሥራ መሥራት እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

በተለይም ማህበራዊ ሚዲያ በጥሩ ከተጠቀምንበት ጥሩ ጥቅም እንዳለው የሚገልፁት መምህሩ፣ ብዙ ከፋፋይ ነገሮች እየተሠሩበት እንዳለና በዚህ ልክ ወደ አንድ የሚያመጡን ጉዳዮች ላይ ብንሠራበት የተሻለ ይሆናል ይላሉ፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ወዘሪት ሕይወት ዮሐንስ በበኩላቸው መገናኛ ብዙሃን ሠብዓዊ መብቶች፣ መልካም አስተዳደርና ሰላም ግንባታ ላይ በትኩረት መሥራት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

ሠብዓዊ መብትን በተመለከተ በተለይም ግጭት ያለባቸው አካባቢዎች ለሚኖር ማህበረሰብ ሠብዓዊ መብቶቹ ምን ምን እንደሆኑ ግንዛቤ የሚፈጥሩለት መገናኛ ብዙሃን ሊኖሩ ይገባል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች መገናኛ ብዙሃን የምርመራ ጋዜጠኝነትን ታሳቢ ያደረገ ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባም ይጠቁማሉ፡፡

መገናኛ ብዙሃኑ ነፃና ገለልተኛ ከመሆን አኳያ ራሳቸውን ሊፈትሹ እንደሚገባም ጠቁመው ፣አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸውንና ለግጭት ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦችን ማካተት እንዳለባቸው ይገልፃሉ፡፡

መገናኛ ብዙሃንና መልካም አስተዳደርን በተመለከተም መገናኛ ብዙሃን መብትና ግዴታውን አውቆ የሚሞግት ማህበረሰብ ማብቃት አለባቸው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም በኃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች ቃል የገቡአቸውን ጉዳዮች ስለመፈፀማቸው የማረጋገጥ ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባም ይጠቁማሉ፡፡




መገናኛ ብዙሃን ግጭት አቀጣጣይ የሆኑ ቃላቶች ላይ ሊጠነቀቁ እንደሚገባ የሚገልፁት መምህሯ፣ የሰላም ግንባታ ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባቸው ያስረዳሉ፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ከሁሉም በፊት የሀገራዊ ምክክርን ፅንሰ ሃሳብ ማወቅ አለባቸው የሚሉት ደግሞ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህሩ ለገሰ በላይ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

እንደእርሳቸው አባባል ጋዜጠኛው ይህ የሀገራዊ ምክክር ሂደት ከሌሎች የግጭት መፍቻ ሂደቶች በምን ይለያል የሚለውን ማወቅ አለበት፡፡ ሀገራዊ የምክክር ሂደቱን እንደ ድርድርና እንደ ሽምግልና እየቆጠረ ላለው ማህበረሰብም ማሳወቅ አለበት ይላሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር ግጭቱን ከሚያባብሱ ይልቅ የሚቀንሱ ዘገባዎችን መሥራት እንደሚኖርበትም ይጠቁማሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የመረጃ ምንጮቻችን ሁልጊዜ የመንግሥት አካላት ብቻ ከሆኑ አካታችነትን ማረጋገጥ አንችልም፡፡ በተለይም ከቋንቋ አጠቃቀም አኳያ እነሱ እና እኛ የሚባል ነገር አሁንም ድረስ እንዳለ ጠቁመው፣ ይህ ድርጊት የታሰበውን ዓላማ እንዳያደናቅፍ ስጋት አለኝ ይላሉ፡፡

የግጭት መንስኤዎችን ከስር መሠረቱ ነቅሶ ለውይይት ማምጣት እንዳለበት እንዲሁም የማህበረሰቡን አመኔታ ማግኘት እንደሚኖርበትም ያብራራሉ፡፡


አባገዳ ሹምቡሉ ዲኮ


ሀደስንቄ ፉሮ አሾ


አባ ገዳ ቡሹሼ ቡታሞ


ሀደስንቄ ሪሀና

# “ምክክሩ ለሀገር ዘላቂ ሰላም መስፈን ዕድል ይዞልን መጥቷል”

- አባገዳዎች እና ሀደስንቄዎች

**መዓዛ ማሞ**

**ዜና ሀተታ**

አባገዳ ሹምቡሎ ዴኮ የአርሲ ሊጣ አባገዳ ናቸው። አባገዳ ሀገር ሰላም እንድትሆን መሥራት ከፈጣሪ የተሰጠው ድርሻ ነው ይላሉ። ለሀገር ሰላም እና አንድነት ለማምጣት በሚደረገው ሀገራዊ ምክክር አስተዋጽኦ ማድረግ ግዴታቸው መሆኑን ፤ ምክክሩ እንደ ሀገር ያሉብንን ያለመግባባት ችግሮች የምንፈታበት ትልቅ ዕድል ይዞ መምጣቱን ይናገራሉ።

ኢትዮጵያውያን በሀገራዊ ምክክሩ የእኔ ሃሳብ ብቻ ተቀባይነት ማግኘት አለበት ሳንል የሌሎችን ሃሳብ በማክበር እና በመደማመጥ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ማበጀት አለብን የሚሉት አባገዳ ሹምቡሎ፤ እንደአባገዳ በሀገራዊ ምክክሩ ሃሳባቸውን በመስጠት እንዲሁም ምክክሩ በተሳካ መልኩ እንዲከናወን እንደሚሠሩም ይናገራሉ።

ፉሮ ኡሾ ደግሞ ከሻሸመኔ ወረዳ የመጡ ሀደስንቄ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ሀደስንቄነት ከፈጣሪ የተሰጣቸው ሰላምን የማውረድ ሥልጣን ነው። በወንድማማቾች መሀከል ሰላም እንዲሆን፣ ደም መፋሰስ እንዳይኖር እና ፍቅር እንዲወርድ መሥራት ሀደስንቄዎች የሚታወቁበት እንደሆነም ይናገራሉ።

ሀደስንቄዎች አለመግባባት ሲኖር በትራችንን አስቀምጠን በምክክር እንዲፈታ እናደርጋለን የሚሉት ሀደስንቄዋ፤ በሀገራችን ያለውን አለመግባባት ለመፍታት በሚደረገው ሀገራዊ ምክክርም ያለንን ተቀባይነት ተጠቅመን የበኩላችንን ለማድረግ ተዘጋጅተናል ነው ያሉት።

የአርሲ ሊጣ አባገዳ የሆኑት ቡሹሼ ቡታም የሀገራዊ ምክክሩ ተሳታፊ ናቸው። እንደ አባ ገዳ በአካባቢያቸው በተሰጣቸው ክብር ጥፋቶች ሲኖሩ በመገሰጽ እንዲሁም አለመግባባቶች ሲኖሩ ሲፈቱ መቆየታቸውን ያወሳሉ። አለመግባባቶች ሲኖሩ በውይይት መፍታት ለኢትዮጵያውያን አዲስ እንዳልሆነም ይናገራሉ።

በመመካከር የማይፈታ ችግር የለም የሚሉት አባገዳው፤ እንደ ሀገር ቁጭ ብለን ስንመካከር ያልተግባባንባቸውን ነገሮች በመፍታት ግጭቶችን እና አላስፈላጊ ጦርነቶችን እናስቀራለን ይላሉ።

ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል በማሳተፍ እያደረገ ያለውን የምክክር ሂደት የሚያደንቁት አባገዳው፤ ያሉ ችግሮችን ፊትለፊት ተገናኝቶ በመመካከር እና በመከባበር ችግሮች እንደሚፈቱ ነው የገለጹት።

ጥላቻ ጠፍቶ እና መከባበር ሰፍኖ ማየት የዘወትር ፍላጎቴ ነው የሚሉት አባገዳው፤ ሀገራዊ ምክክሩ ይህንን የሚያሳካ በመሆኑ እንደአባገዳ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ከፈጣሪ የተሰጠኝን ኃላፊነት እወጣለሁ ይላሉ።

ሪሀና ሀሰን ደግሞ ከሀረርጌ ቦኬ ለሀገራዊ ምክክሩ የአጀንዳ ማሰባሰብ መድረክ አዳማ የተገኙ ሀደስንቄ ናቸው። ሀገራዊ ምክክሩ ተሰባስበን በሀገራችን ባሉ ችግሮች ላይ እንድንመካከር ትልቅ እድል ሰጥቶናል የሚሉት የሀረርጌዋ ሀደስንቄ፤ እድሉ እንዳይባክን እንደሀደስንቄ የበኩሌን አደርጋለሁ ይላሉ።

ሰላም ሁሉም አብዝቶ የሚፈልገው ነገር ነው የሚሉት ሀደስንቄ ሪሀና፤ ሰላም እንዲመጣ ሁሉም ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት እንደሚመክሩም ይገልጻሉ።

በኢትዮጵያ ባህል የማህበረሰብ መሪዎች ትልቅ ክብር አላቸው። ጸብ ቢፈጠር በማስታረቅ፣ ጥፋት ተሠርቶ ቢመለከቱ በመቆጣት ይታወቃሉ። ወጣቶችን በመምከር እና በመገሰጽም መስመር የማስያዝ ሃላፊነት ማህበረሰቡ ሠጥቷቸዋል ሲሉም አባገዳዎች እና ሀደስንቄዎች ያመለክታሉ።

በኦሮሚያ ባህል አባገዳዎች እና ሀደስንቄዎች በማህበረሰቡ በተሰጣቸው ሃላፊነት በተለይ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በመምከር እና ሰላም እንዲወርድ በማድረግ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ይታወቃል።

# ለአትሌቲክሱ ማን ምን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ችግሮች ውስጥ በተዘፈቀበት በዚህ ወቅት ፌዴሬሽኑን በቀጣይ አራት ዓመታት በመሪነት የሚያገለግሉ ግለሰቦች ይመረጣሉ።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን 28ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ዛሬና ነገ ሲያካሂድ፣ ጉባዔው የፌዴሬሽኑን ፕሬዚዳንት ጨምሮ የሥራ ዘመኑን ያጠናቀቀውን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአዳዲስ አመራሮች ይተካል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ስፖርቱን ለመምራት በምርጫው እጩ ሆነው የቀረቡ ግለሰቦች የምረጡኝ ዘመቻ ተጧጡፏል፡፡ አትሌቲክሱን ካለበት ችግር ማውጣት የሚችል ትክክለኛውን ሰው ዘንድሮም ላያገኝ እንደሚችል ስጋቶች ባንዣበቡበት ምርጫ ተስፋ ሰጪ ነገሮችም አልታጡም።

ከዚህ ቀደም ስፖርቱን ለመምራት በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ መራጮች የእጩዎችን ማንነት ጠለቅ ብለው ሳያውቁና ሳይመረምሩ ድምፅ የሚሰጡበት ሁኔታ አትሌቲክሱ አሁን ለሚገኝበት ችግር አንዱ ምክንያት ነው። ዘንድሮ በተለይም ለፕሬዚዳንትነት የሚወዳደሩ እጩዎች ቀደም ብለው የምረጡኝ ቅስቀሳዎችንና በስፖርቱ ለመሥራት የሚያስቡትን እቅዶች በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ሲያቀርቡ ሰንብተዋል። ይህም መራጮች ለማን ድምፅ መስጠት እንዳለባቸው በቂ ጊዜና ግንዛቤ እንዲያገኙ እድል ይፈጥራል ተብሎ ታምኖበታል።

ከፕሬዚዳንታዊ እጩዎቹ መካከል የቀድሞው ውጤታማ አትሌት ገብረእግዚአብሄር ገብረማርያም ትግራይ ክልልን ወክሎ ይወዳደራል። ከ2003-2007 ዓ.ም የአትሌቶች ተወካይና ከ2009- 2013 ዓ፣ም ደግሞ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን ያገለገለው ገብረእግዚያብሔር ወደ ፌዴሬሽኑ አመራርነት ለመመለስ ሲወስን በስፖርቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማስተካከል መሆኑን ይናገራል። በርካታ ጀግና አትሌቶችን ያፈራው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሁን ያለበት ሁኔታ የማይመጥነው በመሆኑ በፕሬዚዳንትነት ቢመረጥ ዘመኑን በዋጀ መልኩ ለመምራት እቅድ እንዳለውም ያስረዳል።

ከእቅዶቹም መካከል በተለይ ሕግና ደንብን አክብሮ ለመሥራት ትኩረት ያደረጉ ሥራዎችን ለማከናወን መዘጋጀቱን በመጠቆምም፣ ዘመኑ የሚጠይቀውን የአትሌቲክስ ነባራዊ ሁኔታ መከተል አስፈላጊ መሆኑን ተናግሯል። የስፖርት ቤተሰቡ ያዘነበትን የአትሌቲክስ ውጤት መመለስ፣ ከሥልጠና ጋር በተያያዘ የሚታየውን ቅሬታ መፍታት፣ ውድድሮችን ማዘመን፣ ለአትሌቶች መለማመጃ የሚሆኑ የማዘውተሪያ ሥፍራዎችን በመገንባት ሰፊ እቅዶችን ይዞ ለፕሬዚዳንትነት ይወዳደራል፡፡ ለነዚህ ዕቅዶቹ መሳካትም ከባለሙያዎች ጋር በቅርበት መሥራት ቀዳሚው ጉዳይ መሆኑንና ቀድሞ በሥራ አስፈጻሚነት ተቋሙን ባገለገለበት ወቅት ተግባራዊ ያልሆኑ በርካታ ጉዳዮችን ወደ መሬት ለማውረድ የተሻለ አቅም ይዞ መመለሱን ገልጿል።

የአማራ ክልል ለፕሬዚዳንታዊ ምርጫው እጩ አድርጎ የወከላቸው የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት የአዲስ አበባ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ያየህ አዲስ በበኩላቸው፣ አትሌቲክስ የኢትዮጵያ መገለጫ ሆኖ ሳለ በሚጠበቀው ልክ ከጊዜው ጋር ማደግ አለመቻሉ በስፖርቱ ያላቸውን ልምድና ዕውቀት ተጠቅመው ለማገልገል እንዳነሳሳቸው ያስረዳሉ። አቶ ያየህ በክልሉ የስፖርት ኮሚሽነር ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፤ ስፖርቱ ቀደም ሲል የነበረበትንና አሁን ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ በማጤን በቀጣይ ምን መደረግ አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ራዕይ አስቀምጠው ፌዴሬሽኑን ለመምራት እንደሚወዳደሩ ተናግረዋል። በፌዴሬሽኑ ውስጥ ሪፎርም በመሥራትና ሊሳኩ የሚችሉ ፖሊሲዎችን በማውጣት ስፖርቱን በሥርዓት ለመምራት የሚያስችል አቅም እንዳላቸውም አብራርተዋል።

እንደ አቶ ያየህ ገለፃ፣ ከተመረጡ በአጭር መካከለኛና ረጅም ጊዜ የሚሳኩ እቅዶችን አዘጋጅተዋል። ቀዳሚው ጉዳይ ስፖርቱን ሊያሳድግ በሚችል ብቃት ያለ አድሎ ፌዴሬሽኑን መምራትም ትኩረታቸው ነው፡፡ በውጤት መጥፋት ያዘነውን ሕዝብ ለመካስ የሚያስችል የ100 ቀናት እቅድም አዘጋጅዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የተከፋፈለውን ባለሙያ በአንድነት እንዲሠራ የሚያስችል አሠራር መፍጠር፣ ምርጥ አትሌቶችን አሰባስቦ ወደ ሥልጠና በማስገባት ለውጤት መሥራት፣ ነባሩን የአትሌቲክስ ባህል መመለስም ትኩረት ከሚሰጧቸው ጉዳዮች ቀዳሚ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ስፖርቱ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው በመሆኑ ከተቋማቱ ጋር በቅንጅት መሥራት፣ አትሌቶችና ሌሎች ባለሙያዎች የሚገባቸውን ማበረታቻ መስጠት፣ ጥፋት የሚፈጽሙትን ሥርዓት ማስያዝ፣ በውጪ ስፖንሰሮች ላይ የተመሰረተውን ሀብት አሰባሰብ ከባለሀብቶች ጋር በመሆን በሀገር ውስጥ እንዲያድግ ማድረግና በአግባቡ ማስተዳደር፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ማሟላት፣ የተጠናከረ የምልመላ፣ የሥልጠናና ውድድር ሥርዓት መዘርጋት፣ የአትሌቶች የህክምና ማዕከል ማቋቋም፣ ፌዴሬሽኑ ከተቋማት ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆኖ በትብብር የሚሠራበትን ሁኔታ ማመቻቸት በረጅም ጊዜ ዕቅዶቻቸው ትኩረት የሚያደርጉባቸው ጉዳዮች እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ወክለው ለፕሬዚዳንትነት የሚወዳደሩት አቶ ዱቤ ጂሎ፣ ከአትሌትነት እስከ ስፖርት ከፍተኛ አመራርነት ለረጅም ዓመታት በዘርፉ አገልግለዋል። በቴክኒክ ባለሙያነት ያገለገሉትን የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሁን ደግሞ በአመራርነት በማገልገል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት እንደሚወዳደሩ የገለፁት አቶ ዱቤ፣ ከፌዴሬሽኑ ለቀው የስፖርት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ሆነው ከተሾሙ በኋላ የተካሄዱ ሶስት ኦሊምፒኮች (የሪዮ፣ ቶኪዮ እና ፓሪስ) የተመዘገቡ አሳፋሪ ውጤቶች እና እሱን ተከትሎ የተፈጠሩ ውዝግቦች ቁጭት ፈጥረውባቸው ፌዴሬሽኑን ለመምራት ወደ ውድድር እንደመጡም ያስታውሳሉ። አትሌቲክስ የኢትዮጵያ መለያ እንደመሆኑ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ የሚያስችል ልምድና የትምህርት ዝግጅት ያላቸውና በዓለም አቀፉ ተቋም ምርጥ ቴክኒካል ዳሬክተርነት እውቅና ያገኙ መሆናቸውም የስፖርቱን ችግር ለመፍታት እንደሚያስችላቸው ይናገራሉ።

"የሥራ ዘመኑን ያጠናቀቀው ሥራ አስፈጻሚ የታየበት መፈረካከስና እርስ በእርስ አለመስማማት፣ የቴክኒክ ኮሚቴው አሠራር እንዲሁም አደረጃጀቱን ለማረም የሚያስችል ዕቅድ ነድፌያለሁ" የሚሉት አቶ ዱቤ፣ ቀዳሚው ሥራቸውም ከፍተኛ ክፍተት የሚታይበትን የፌዴሬሽኑን ጽህፈት ቤት በተገቢው ባለሙያ ማደራጀትና ውድድር የሚመሩና የቴክኒክ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ሙያዊ ኮሚቴዎችን ማደራጀት መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ሀገር እንደመሆኗ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ማዘጋጀት ቢገባትም የስፖርት መሠረተ ልማቶች አለመኖር ወደ ኋላ አስቀርቷታልም ይላሉ። ይህም አትሌቶች ልምምድ የሚያደርጉበትን ቦታ እንኳን አሳጥቷል ባይ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከዓለም አትሌቲክስ እና ሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በአስቸኳይ የመሮጫ መም ለማስገንባት ጥረት እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል።

ከሴቶች ተሳትፎ አንጻር በተለይ በአሠልጣኝነት በማብቃትና የታዳጊ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት ላይም ትኩረት ለማድረግ እንደሚሠሩም አክለዋል። ከምርጫው ጋር ተያይዞም ድምጽ የሚሰጡ የጉባዔው አባላት ግለሰብን ሳይሆን ሀገርን በመመልከት ለስፖርቱ ተገቢውን ሰው መምረጥ እንዳለባቸውም አቶ ዱቤ አደራ ብለዋል።

በፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ፉክክሩ እጩ ሆነው ከቀረቡና የአሸናፊነት ግምት ከተሰጣቸው መካከል የኦሮሚያ ክልልን የወከለው የቀድሞው ጀግና አትሌት ስለሺ ስህን ዋነኛው ነው። የኢትዮጵያ አትሌቶች ማህበርን በፕሬዚዳንትነት ያገለገለው ስለሺ ፌዴሬሽኑን ለመምራት ምን እቅድ እንዳለው ለመጠየቅ በተደጋጋሚ ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም ጥያቄ ፍቃደኝነት ማጣት ከሕዝብ ፍላጎት እና ተስፋ በተቃርኖ መቆም ነው!

የሰላም ጉዳይ በየትኛውም የዓለም አካባቢ የሚገኝ ማኅበረሰብ የሁሌም ጥያቄ ነው። አይደለም ነገን ዛሬን በአግባቡ ለመኖር ሰላም ለመላው የሰው ልጅ ፤ ከዚያም አልፎ ለዓለም ወሳኝ ጉዳይ ነው። ከዚህም የተነሳም የሰላም ጉዳይ የሰው ልጅ ዋነኛ የዕለት ተዕለት አጀንዳ ነው ። ስለሰላም የሚጮሁ ድምጾችም በየጊዜው ጎልተው መደመጣቸው የተለመደ ነው።

በቀደሙት ዘመናት በአንድም ይሁን በሌላ የሰውን ልጅ አጠቃላይ ሰላም የሚያናጉ እና ህልውናውን ጭምር ስጋት ውስጥ የከተቱ ዓለም አቀፍ ክስተቶች ተፈጥረዋል። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በተቀሰቀሱ ግጭቶች እና ጦርነቶች ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል ያልተገደደ ማኅበረሰብም የለም። ተወደደም ተጠላም እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ከሰላም እጦት ፤ ከግጭት እና ከጦርነት ጋር የተያያዘ ትርክት አለው።

አብዛኛው የዓለማችን ሕዝብ ከነዚህ የግጭት እና የጦርነት ታሪኮች ተገቢውን ትምህርት በመውሰድ፤ ለግጭት ገፊ የሆኑ ምክንያቶችን በውይይት እና በድርድር የመፍታትን መንገድ ዋና አማራጭ አድርጎ ወስዷል። በዚህም ከግጭት እና ግጭት ሊያስከፍል ከሚችለው ያልተገባ ዋጋ ራሱን ታድጎ ፤ የሰላም ዋነኛ ትሩፋት በሆነው ልማት ራሱን አበልጽጓል።

እኛም እንደ ሀገር ያለን እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም ። የረጅም ዘመን የሀገረ- መንግሥት ግንባታ ታሪክ ባለቤቶች ነን ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ ተጉዘናል። ግጭቶች እና ጦርነቶች የታሪካችንን ሰፊውን ምዕራፍ የሚሸፍኑ ናቸው። በዚህም ከአንድ ትልቅ ታሪካዊ ከፍታ ወርደን ዛሬ የምንገኝበት የቁጭት የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንገኛለን።

ሕዝባችን በአብዛኛው አማኝ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለሰላም ያለው እሳቤ ሆነ ከእሳቤው የሚመነጨው የዕለት ተዕለት ሕይወቱ ለሰላም ትልቅ ሥፍራ የሚሰጥ ነው። አብዝቶ ስለሰላም የሚሰብክ እና የሰላም ሀዋሪያነት የተላበሰ ነው። ከኅብረ-ብሄራዊ ማንነቱ ጋር በተያያዘም ለሰላም የቆሙ እና ሰላምን የሚያጸኑ የተለያዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ባለቤትም ጭምር ነው።

በየዘመኑ የሚከሰቱ አለመግባባቶች ከፈጠሯቸው ግጭቶች እና ጦርነቶች ጋር በተያያዘ ከከፈላቸው ያልተገቡ ዋጋዎች አንጻርም ፤ ስለሰላም ያለው አቋም በየትኛውም ሁኔታ የጸና ነው። ሰላም የእስትንፋስ ያህል አስፈላጊ ስለመሆኑ ፤ በተለያዩ ወቅቶች በተፈጠሩ ግጭቶች እና ጦርነቶች በብዙ መማር ችሏል። በዚህም በየትኛውም ሁኔታ እና አጋጣሚ የሚፈጠሩ ግጭቶች እና ጦርነቶችን የሚያወግዝበትን አቅም ገንብቷል።

በየትኛውም ክፍል ያለ ኢትዮጵያዊ በአንድም ይሁን በሌላ የግጭት እና የጦርነትን አስከፊነት ያውቃል፤ ከታሪክ ትርክት ባለፈ ፤ በሕይወት ዘመኑ የችግሩን አስከፊነት በተጨባጭ ማየት ችሏል። የዕለት ተዕለት ሕይወቱ በብዙ ፈተናዎች እና ተገማች ባልሆኑ አደጋዎች ሰለባ ሆኖ በተጨባጭ አይቶታል።

በብዙ ልፋትና ምጥ ወልዶ ያሳደጋቸውን ልጆቹን አጥቷል ፤ በብዙ ድካም እና ላብ የገነባቸው የልማት መሠረተ ልማቶቹ ድንገት ወደ ፍርስራሽነት ተለውጠው አይቷል። ለዓመታት የገነባው ቤት ንብረቱ እና ቤተሰቡ ተበትነው ለስደት የተዳረገበት አጋጣሚ ፤ በአንድ ምሽት የዘመናት ተስፋውን ተነጥቆ በሕይወት ግራ መጋባት ውስጥ ያለፈባቸውን ቀናቶች አይረሳውም።

ሕዝባችን ዛሬ ላይ በየአደባባዩ እየወጣ ስለሰላም የሚያሰማው ድምጽ ከዚህ ሁሉ የትናንት እና የዛሬ የሕይወት ተሞክሮው የመነጨ ፤ እንደሀገር ካለፍናቸው የትናንት ውድቀት እና የማነስ ታሪክ በመነሳት ነው። ዛሬ ላይ ቆሞ ተስፋ ስለሚያደርጋቸው ነገዎች ዘብ በመቆም ነው።

ይህንን የሕዝብ የሰላም ድምጽ ለመስማት ፈቃደኝነት ማጣት ከራስ ማንነት ጋር መጣላት ብሎም ከሕዝብ ፍላጎት እና ተስፋ ጋር በተቃርኖ መቆም ነው። የሕዝብ የሰላም ጥያቄን አሳንሶ ማየትም ፤ ከሁሉም በላይ በሕዝቡ ብሩህ ነገዎች እና ተስፋ ላይ በጠላትነት መሰለፍ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## ሕዝብ የሚፈልገው ሰላም ነው

**ሰሞኑን የአማራ ክልል ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ለሰላም ጥሪ አድርጓል፡፡ በግጭት እና በጦርነት መማረሩን በገሃድ ወጥቶ ተናግሯል፡፡ በየጫካው የሚገኙ ቡድኖችም ለሰላም ቅድሚያ እንዲሰጡ መልዕክት አስተላልፏል**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው። ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ሕዝብ ነው። ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው። ከዚህም ባሻገር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መሽቶ በነጋ ቁጥር በሰላም አውለኝ፤ በሰላም አሳድረኝ ብሎ ፈጣሪውን ይማጸናል። ሀገሩም በሰላም ውላ እንድታድር እንደየእምነቱ ይለምናል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰላም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ እና የሰላምን ዋጋ የተረዳ ነው። ሆኖም የዘመን ጉድ የሆኑ ፖለቲከኞች ነን ባዮች የዚህን ኩሩ ሕዝብ የዘመናት ዕሴቶች ለመናድ ሲሯሯጡ ይታያሉ። ልዩነቶችን ጌጡ አድርጎ የኖረውን ሕዝብ እርስ በእራሱ እንዳይተማመን እና እንዲጋጭ የሚያደርጉ ትርክቶችን በመፍጠር በሀገሪቱ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነግስ ያለመታከት በመሥራት ላይ ይገኛሉ። እገሌ ነጻ አውጪ የሚል ታፔላ በመለጠፍ ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ ለማባላት ሲታትሩም ይታያሉ።

በዚህም የዜጎችን በሰላም የመኖር መብት አደጋ ላይ የጣሉና የሀገርን ሰላምና ደህንነት የሚያውኩ ሙከራዎችም ተከስተዋል። በወለጋ፣ በሶማሌ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በመተከልና በደቡብ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በእነዚሁ የጥፋት ኃይሎች አማካኝነት በርካታ ዜጎች ተገድለዋል፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ለአስከፊ ሕይወት ተጋልጠዋል።

ከሁለት ዓመታት በፊት በትግራይ ደም አፋሳሽ ጦርነት ተካሂዶ በርካታ የሰው ሕይወት እና የሀገር ሀብት ጠፍቷል። በጦርነት አሸናፊ መሆን አይቻልም እና ችግሩን በድርድር ለመፍታት ተችሏል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በትግራይ ዘላቂ ሰላም ለማስገኘት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል። በተለይም መንግሥት በጦርነቱ በእጅጉ የተጎዳውን የትግራይ ሕዝብ መልሶ ለማቋቋምና ጦርነቱ ያሳረፈበትን ሥነልቦና ለማከም በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ከስምምነቱ መፈረም በኋላ የጥላቻውን ጉም በመግፈፍ ወደ ትግራይ በግንባር ቀደምነት የተጓዘው በአፈ ጉባዔው የተመራው የፌዴራል መንግሥቱ ልዑክ ነበር። ይህ ልዑክ ከተጓዘ በኋላ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የባንክና የአውሮፕላን አልግሎቶች በፍጥነት እንዲጀምሩ ተደርገዋል።

የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር በተመሠረተ ጊዜ መሳሳብና መጓተትን ለማስቀረት ሲባል የአመራሩን ድርሻ ክልሉ እንዲወስድ በማድረግ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ፋታ አግኝቶ ፊቱን ወደ ሰላምና ልማት እንዲያዞር ተደርጓል።

የግብርና ሥራውን ለማገዝ የሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በክልል ደረጃ ከሚጠበቅበት በላይ ሠርቷል። ዩኒቨርሲቲዎችንና ትምህርት ቤቶችን ወደ አገልግሎት ለመመለስ የትምህርት ሚኒስቴር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። በክልሉ ተቋርጦ የነበረውን ትምህርት እንዲጀመር ከማድረግ ባሻገር ከሁለት ዓመታ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ተማሪዎች እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል።

የመከላከያ ሠራዊት የሕዝቡን ችግር ለመፍታት ከራሱ በጀት ቀንሶ አያሌ ተግባራት አከናውኗል። የሰላም ስምምነቱን እንደ ዕድል በመጠቀም ሕዝብን ከችግር በማዳን፣ መንግሥታዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማስጀመር ኃላፊነቱን ተወጥቷል። ከፌዴራል መንግሥቱም አልፎ ክልሎች ከአነስተኛ በጀታቸውና ገቢያቸው በመቀነስ የትግራይ ክልልን ደግፈዋል። ይህ ሁሉ ጥረት ዛሬ ፍሬ ማፍራት ጀምሯል።

በአሁኑ ወቅት ወደ ሰላም የተመለሰው የትግራይ ክልል በጦርነት ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸውን ወጣቶች ወደ መደበኛ ሕይወታቸው እንዲመለሱ እያደረገ ይገኛል። በአሁኑ ወቅትም በክልሉ 75 ሺህ የቀድሞ ተዋጊዎችን በአራት ወራት ውስጥ በተሃድሶ ሥልጠና ወደ ማኅበረሰቡ የመመለስ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

በኦሮሚያ ክልልም ባለፉት ዓመታት በርካታ ግጭቶች ተካሂደዋል። በዚህም የበርካታ ንጹሃን ሰዎች ሕይወት ተቀጥፏል፤ ንብረት ወድሟል፤ ሕዝብ ተፈናቅሏል፤ በአጠቃላይ አለመረጋጋት ተከስቶ ቆይቷል። ሆኖም በተደረጉ ጥረቶች እራሱን የኦሮሞ ነጻ አውጪ ሠራዊት ብሎ የሚጠራው አካል ለሰላም ቀናኢ ሆኖ ተገኝቶ ሰሞኑን ፊቱን ወደ ሰላም መልሷል። በዚህም ክልሉ የተረጋጋ ሰላም አግኝቷል፤ የሰላም አየር መንፈስ ጀምሯል። ይህ ቡድኑ የወሰደው የሰላም አማራጭ ለሌሎች በጫካ ለሚገኙ ቡድኖች ትልቅ መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው።

በተመሳሳይም በአፋር ክልል ለረጅም ጊዜያት ያህል የትጥቅ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ አካላትም የሰላም መንገድ መርጠው ተመልሰዋል። በተመሳሳይም የቅማንት እና ጉሙዝ ታጣቂ ችግሮቻችን የሚፈቱት በሰላም እንጂ በጦርነት አይደለም በሚል መሣርያቸውን አስቀምጠው ማረሻ እና ሞፈር ጨብጠዋል።

የእነዚህ ቡድኖች ድርጊት የሚበረታታ እና የሚመሰገን ነው። አሉ የሚባሉ ጥያቄዎችን በመሣርያ ኃይል ማስመለስ እንደማይቻል እና ችግሮችን በውይይት መፍታት እንደሚቻል ያሳየ ድርጊት ስለሆነ በአርአያነቱ የሚታይ ነው። ለሕዝብ ቆመናል የሚሉ አካላት በመጀመርያ የያዙትን መሣርያ አስቀምጠው የሕዝብን በሰላም ወጥቶ የመግባት መብት ማረጋገጥ አለባቸው። ይህ ሲሆን ለሕዝብ መቆማቸውን ማሳየት ይችላሉ።

ከዚህ በተቃራኒ ሕዝብን እየዘረፉ እና እያዋረዱ አለፍ ሲልም እየገደሉና እያቆሰሉ ለሕዝብ ቆመናል የሚል መታበይ በመጨረሻ የሚያስከትለው ውርደትን ነው። ስለዚህም በየጫካው መሳርያ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ለሕዝብ ክብር ሊሰጡ ይገባል። በሕዝብ ስም እየማሉ እና እየተገዘቱ ለሕዝብ ቆመናል ማለት ጊዜ ያለፈበት ፋሽን መሆኑን መረዳት ይገባል። ሰሞኑንም በአማራ ክልል የታየው ሀቅ ይኸው ነው።

ሰሞኑን የአማራ ክልል ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ለሰላም ጥሪ አድርጓል። በግጭት እና በጦርነት መማረሩን በገሃድ ወጥቶ ተናግሯል። በየጫካው የሚገኙ ቡድኖችም ለሰላም ቅድሚያ እንዲሰጡ መልዕክት አስተላልፏል። ባለፉት ዓመታትም በግጭቱ ምክንያት ታሞ መታከም እንዳልቻለ፤ ልጆቹን ትምህርት ቤት መላክ እንዳቃተው፤ አርሶ እራሱን እና ልጆቹን መመገብ እንደተሳነው በምሬት ገልጿል። ቆመንለታል የሚሉ አካላትም በጥቅሙ እና በእድገቱ ላይ እንደቆሙበት ተናግሯል።

ስለዚህም የሕዝብን ጥሪ እና የሰላም መልዕክት መቀበል የግድ ሊል ይገባል። ከሕዝብ በላይ አዋቂ ከሕዝብ በላይ መስካሪ የለም። ጦርነት በቃኝ ፤ ሰላም ናፈቀኝ ካለ መብቱ ሊከበርለት ይገባል። ሕዝቡ ጥቅሜ የሚከበርልኝ በጦርነት ሳይሆን በምክክር ነው ካለ የሕዝቡ ፍላጎት ቅድሚያ ሊሰጠው የግድ ነው።

ሕዝብ ሁልጊዜም ቢሆን ትክክል ነው። ሕዝብ ምንጊዜም ቢሆን ሰላም ፈላጊ ነው። ስለዚህም ከሕዝብ ፍላጎት ውጪ የራስን ፍላጎት በግድ መጫን ዞሮ ዞሮ ከሕዝብ ጋር ያጋጫል፤ መጨረሻውም አያምርም። የአማራ ክልል ሕዝብም ያስተላለፈው መልዕክት ይኸው ነው። በአደባባይ ሰላም እንደናፈቀው ተናግሯል። ስለዚህም ዛሬ ነገ ሳይባል የሕዝቡ ድምጽ ሊደመጥ ይገባል።

# የጨቅላ ሕፃናት የዓይን በሽታ እልባት ካልተሰጠው በሀገሪቱ የዓይነ ስውራን ቁጥር ይጨምራል

## - በሁለት ሆስፒታሎች ህክምና ካገኙ ህፃናት መካከል 48 በመቶ የችግሩ ሰለባ ናቸው

**ሶሎሞን በየነ**

አዲስ አበባ፡- በጨቅላ ሕፃናት ላይ የሚከሰተው የዓይን ብርሃን ተቀባይ የደም ስሮች መቀንጨር በሽታ በጊዜ እልባት ካላገኘ በቀጣይ ዓመታት በሀገሪቱ የዓይነ ሥውራን ቁጥር በእጅጉ እንደሚጨምር ተገለጸ። በሁለት ሆስፒታሎች ሙቀት ክፍል ተኝተው ህክምና ሲያገኙ ከነበሩ ህፃናት መካከል 48 በመቶ የችግሩ ሰለባ መሆናቸውን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ህክምና ትምህርት ቤት በዓይን ህክምና ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር እንዲሁም በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል የአዋቂና የህፃናት ዓይን ህክምና ልዩ ስፔሻሊስት ሀኪም ዶክተር ሳዲቅ ታጁ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ የእናቶችና ህፃናት የጤና አገልግሎት መሻሻል ጋር ተያይዞ መወለድ ከሚገባቸው ጊዜ ቀደም ብለው የሚወለዱ ጨቅላ ሕፃናትን ሕይወት ከመታደግ አኳያ አመርቂ ውጤት ቢመዘገብም፤ በዓይን ብርሃን ተቀባይ የደም ስሮች መቀንጨር በሽታ ሳቢያ የዓይን ብርሃናቸውን የሚያጡ ጨቅላ ህፃናት ቁጥር በእጅጉ እየጨመረ ነው።

እ.ኤ.አ ከ1920-30ዎቹ የዓለም የጤና አብዮት ማበቡን ተከትሎ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የእናቶችና ህፃናትን ሕይወት መታደግ መቻሉን ዶክተሩ ጠቁመው፤ ይሁን እንጂ ሕይወታቸው ተርፎ የዓይን ብርሃናቸውን በሚያጡ ጨቅላ ህፃናት ሳቢያ ያደጉ ሀገራት በ1950ዎቹ በዓይነ ስውራን ተጥለቅልቀው እንደነበር አውስተዋል።

“ይህ ችግር በኛ ሀገርም እንዳይከሰት ስጋት አለኝ” ያሉት ዶክተር ሳዲቅ፤ ለችግሩ በጊዜ እልባት ካልተሰጠው በሚቀጥሉት አምስት እና 10 ዓመታት ውስጥ በዚህ በሽታ ብቻ በሀገሪቱ 20 ሺህና 30 ሺህ ዜጎች ዓይነ ስውር እንደሚሆኑ ጥናቶች ያመላክታሉ ብለዋል።

በሀገሪቱ አሁን ባለው ሁኔታ ህክምናው በጥቁር አንበሳ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታሎች እና በተወሰኑ የግል ጤና ተቋማት ብቻ እንደሚሰጥ ያመለከቱት ዶክተር ሳዲቅ፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ በተደረገ ጥናት በጥቁር አንበሳና ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታሎች የጨቅላ ህፃናት ማቆያ ሙቀት ክፍል ተኝተው ህክምና ሲያገኙ ከነበሩ ጨቅላ ህፃናት መካከል 48 በመቶ (መጠኑ ቢለያይም) የችግሩ ሰለባ ሆነው መገኘታቸውን አስታውቀዋል።

በሁለቱ ተቋማት ብቻ ይህን ያህል የበሽታው ተጠቂ ህፃናትን ማግኘት ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ ችግሩ ምን ያህል የገዘፈ እንደሆነ መገመት ቀላል ነው ያሉት ዶክተሩ፤ እነዚህ ህፃናት በጊዜው በመታየታቸው ብርሃናቸውን መታደግ መቻሉን ተናግረዋል።

ዶክተር ሳዲቅ፤ ችግሩ ቀድሞ ከተደረሰበት የህፃናትን የዓይን ብርሃን መታደግ እንደሚቻል አስረድተው፤ ሕጻናቱ ከተወለዱ በሁለትና ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ችግሩ ያለባቸው መሆኑ ተለይቶ ህክምናውን ካላገኙ፤ የዓይናቸውን ብርሃን መመለስ እንደማይቻል ገልጸዋል።

በሀገሪቱ ህፃናት የዓይን ብርሃናቸውን ባጡ በዓመቱ 60 በመቶዎቹ ሕይወታቸውን እንደሚያጡ ጥናቶች ያሳያሉ ያሉት ዶክተሩ፤ ስለበሽታው በቂ እውቀትና ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት ሕይወታቸው ተርፎ የዓይን ብርሃናቸውን የሚያጡ ጨቅላ ህፃናት ቁጥር እየጨመረ ነው። እነዚህ ህፃናት ደግሞ በሕይወት የመኖር ተስፋቸው የመነመነ ነው ብለዋል።

ያደጉ ሀገራት ካጋጠማቸው የህፃናት ዓይነ ስውርነት ማዕበል በኋላ በሙቀት ክፍሎቻቸው ከሚሰጠው የጨቅላ ህክምና ጋር ተያይዞ የዓይን ብርሃን ተቀባይ የደም ስሮች መቀንጨር ልየታና የዓይን ምርመራ እንደ አንድ የህክምና ክፍል አድርገው እየሠሩበት እንደሚገኙ አመላክተው፤ በዚህም ችግሩን መከላከል መቻላቸውን ያስረዳሉ።

ዶክተሩ፤ ከሌሎች ሀገራት ትምህርት በመውሰድ ተመሳሳይ ርምጃ በመውሰድና ለችግሩ ትኩረት በመስጠት የህፃናትን ሞት የመቀነስ ግብ የህፃናት ዓይን ብርሃን መታደግን ታሳቢ ካላደረገ በቀጣዩ ትውልድ እንዲሁም በሀገር ትልቅ ችግር መፍጠሩ እንደማይቀር አሳስበዋል።

ይህ እንዳይከሰት ትምህርት ክፍሉ በበኩሉ ችግሩን ቀድሞ መለየትና መከላከል የሚቻልበት የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በህፃናት ሙቀት ማቆያ ክፍል የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ችግሩን መለየት እንዲችሉ የማሠልጠን እንዲሁም ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ችግሩን የመለየት ሥራ እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

# የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ባንኮቹ ሊሠሩ የሚችሉትንና የማይችሉትን በዝርዝር ማስቀመጡን ይናገራሉ፡፡ የአዋጁ አቀራረብ ባንኮቹ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርግ የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ወደፊት ተግባራዊ ሲሆን የሚታይ ነው፡፡ የለውጡ ሂደት አንዱ አካል ስለሆነ ግን አዋጅ መውጣቱ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

የአዋጁ ይዘት አቅጣጫ ገና ግልጽ ሆኖ አልተቀመጠም የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ አንዳንድ ነገሮቹ ወደፊት የሚታዩ ሆነው፤ ባለበት ሁኔታ ስናየው የውጭ ባንኮችን ለመሳብ በር የመክፈቱን ያህል፤ በባንኮቹ አሠራር ላይ ገደብ የጣሉ ይዘቶች ስላሉት፤ እነዚህ ይዘቶች ማነቆዎች እንዳይሆኑ ስጋት መኖሩን ይናገራሉ፡፡

የውጪ ባንኮቹ አዋጁን ተከትለው ወደ ሀገር ውስጥ ይመጣሉ ወይ አንዱ ጥያቄ ነው የሚሉት አቶ ከቡር ገና፤ አዋጁ እንዲመጡ ታስቦ የተዘጋጀ በመሆኑ ይመጣሉ የሚል እምነት አለ። ቢመጡም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባንኮች አብዛኞዎቹ በአማካይ ከ20 ዓመት በላይ እድሜ የሆናቸው ስለሆነ በቆዩባቸው ዓመታት ውስጥ በርካታ ለውጥ አሳይተዋል፡፡ ባንኮቹ ቢመጡም ለመወዳደር የሚያስቸግራቸው አይመስለኝም። ቴክኖሎጂውንም ገዝተው ማምጣት፤ በዘርፉ እውቀትና ልምድ ያላቸውን ሰዎች ቀጥሮ ማሠራት ይችላሉ ብለዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ኃይለመስቀል ጋዙ በበኩላቸው፤ ሌላ ሀገር ያለው የባንክ አሠራርና ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የባንክ አሠራር ባህሉ አንድ አይነት ባለመሆኑ፤ የውጭ ባንኮች ጫና ሊፈጥርባቸው ይችላል ይላሉ፡፡ ችግሩ የባንክ አስተዳደሩን በተወሰነ መልኩ ሊፈትን ስለሚችል ለመግባትም ፈተና ሊሆንባቸው እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

በዘርፉ ምርጥ ተሞክሮ ያላት ህንድ ስትሆን 46 የሚደርሱ የውጭ ባንኮችን በመያዝ የባንክ ኢንዱስትሪውን በስፋት የገነባች ሀገር ናት፡፡ የሀገሪቱ ተሞክሮ አዋጁ ከመጽደቁ ባሻገር ወደ ተግባር እንዲገባ ማድረግ እንደሚገባ አመላካች ነው፡፡ በጎጥና በብሔር የተደራጁ ባንኮች ወደ አንድ ሊመጡ የሚችሉበት ዕድልን ይፈጥራል፡፡ ይህም ሆኖ የሀገር ውስጥ ባንኮች መዋሃድ ካልቻሉ ምን አልባትም ፈተና ላይ ሊወድቁ ይችላሉ ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

አቶ ከቡር በበኩላቸው፤ የውጪ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸው ከጥቅሙ ባሻገር ስጋት እንዳለው ይናገራሉ። የውጭ ባንኮች ጠቅላላ ገበያውን ከተቆጣጠሩት የሀገሪቷን የወደፊት አቅጣጫ የሚመሩት እነሱ ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ ሰፊ ይሆናል፡፡ ለዚህም አፍሪካ ውስጥ ፈጽሞ የሀገር ውስጥ ባንክ የሌለባቸውን ፤ በውጭ ባንኮች የተዋጡ ሀገራትን በዋቢነት ይጠቅሳሉ፡፡ የውጭ ባንኮች ዋና ፍላጎት በሀገር ውስጥ ልማት ማምጣት ሳይሆን ለባለቤቶቹ እና ለባለአክሲዮኖቹ ትርፍ ማሳደግ ዓላማቸው ነው። ከልማት ይልቅ በተለይም ለውጭ ገበያ ሊቀርቡ በሚያስችሉ ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡

በሌላ መልኩ ባንኮቹ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የሀገር ውስጥ ባንኮች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንደሚያደርግ የሚያብራሩት አቶ ከቡር፤ ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በየጊዜው ቴክኖሎጂን በመቀበልና በማዋሃድ ዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመሥራት መቻሉን በመጥቀስ ባንኮች ከዚህ ተምረው ለመወዳደር ምንም የሚያስቸግራቸው ነገር አይኖርም ባይ ናቸው፡፡

ባንኮቻችን ከስጋት ይልቅ ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፤ የገበያው አቅም፤ ንግዱ እና ኢንዱስትሪው የት አካባቢ እንደሚንቀሳቀስ ከማንኛውም የውጭ ባንክ የበለጠ መረጃ ስላላቸው ተወዳዳሪ መሆን ይችላሉ፡፡ የነሱ መምጣት ሊያሳስብ አይገባም፤ ፖሊሲውም ይህን ለመከላከል ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች መኖራቸውን መመልከትም ተገቢ እንደሆነ ይመክራሉ፡፡

አቶ ከቡር፤ የጸደቀው አዋጅ በአንድ በኩል ወደ ‹‹ሊብራሊዝም›› አልሄደም፤ ወይም ‹‹ዲቨሎፐመንታሊስት›› ወደሚባለው በመሄድ ባንኮችን ለመምራት፤ ተሳትፏቸውን እንዲያሳድጉ የሚፈልግ ሆኖ ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ገበያው የበለጠ ሚና እንዲኖረው ይፈለጋል፡፡ ስለዚህ አቅጣጫው ገና አልተለየም ብለዋል፡፡ የመንግሥት አቅጣጫ የትኛውን እንደሚከተል ገና በግልጽ አልተቀመጠም። ወደ ፊት በገበያው ከመመራት ይልቅ በዕቅድ ለመመራት ትኩረት እንደሚሰጥ ጠቁመዋል፡፡

አዋጁ ግቡን እንዲመታና ሀገርን በኢኮኖሚ ለማሳደግ ውጤታማ የሆኑ ሀገራትን ተሞክሮ መውሰድ እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት አቶ ከቡር፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ ዕድገት ያሳዩ እንደ ቻይና፤ ጃፓን ቬትናም የመሳሰሉ ሀገራትን አሁን ለደረሱበት የዕድገት ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት ገበያው እንዲመራ በማድረግ ብቻ ሳይሆን የለውጥ አቅጣጫው ጭምር በማስቀመጥ ነው፡፡ ዘርፉ እንዲያድግ መንግሥት ትልቅ ሚና መጫወት እንደሚኖርበትም መክረዋል።

ገበያው ይምራው ከተባለ ዕድገቱ ፎቅ በመገንባት ላይ የተገነባ ይሆናል የሚሉት አቶ ከቡር፤ ከሌሎች ሀገራት እንማር ከተባለ መንግሥት ከፍተኛ የመምራት ኃላፊነት ወስዶ ሀገር ለማሳደግ የሚያስችል መንገዶችን በር በመክፈት ለዕድገት መንቀሳቀስ ይገባዋል ይላሉ፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ኃይለመስቀል ጋዙ በበኩላቸው፤ አዋጁ መጽደቁ አንድ ለሀገር እድገት መሠረት የሆነ ታሪካዊ ሁነት ነው። ተሳክቶ ባንኮች ከገቡ ለዘርፉ ብዙ ጥቅሞችን ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከጥቅሞቹ መካከልም ባንኮቹ ሲገቡ ያደገ ቴክኖሎጂ እና የባንክ የአሠራር ሥርዓት ይዘው ይመጣሉ ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት ኢትዮ ቴሌኮም ተወዳዳሪ አለመኖሩ የኔትወርክና ኢንተርኔት ተደራሽነቱ አለመዘመኑ እንደ ቅሬታ ይነሳበት እንደነበር ያስታወሱት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ የሳፋሪኮም ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ለመወዳደር ሲል እንደ ቴሌብር የመሳሰሉ መተግባሪያዎችን በማበልጸግ መሻሻል አሳይቷል፡፡ የውጭ ባንኮች መግባትም በዘርፉ ያለውን ውድድር በማሳደግ አገልግሎቱ እዲሻሻል ያደርጋል። የሀገር ውስጥ ባንኮች ባንክ በሌለባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ገብተው የመሥራት መነቃቃት እንዲፈጥሩ ያነሳሳቸዋል ብለዋል፡፡

የሕጉ መጽደቅ እንደ ሀገር የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ ለመግባት (access to global financial system) ዕድል እንደሚሰጥ የሚያብራሩት አቶ ኃይልመስቀል፤ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ያፋጥናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ መንግሥት የሚገቡ የውጭ ባንኮችን በማበረታታት በሀገር ውስጥ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡ ካልሆነ ግን ያተረፉትን ትርፍ ወደ ውጭ የማውጣት ዕድል ከፍተኛ እንደሚሆን ስጋታቸውን አጋርተውናል፡፡

የሀገር ውስጥ ባንኮች ዕድሉን በአግባቡ በመጠቀም ተወዳዳሪና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ሊሠሩ ይገባል፡፡

# በኦሮሚያ ክልል ሁለት ነጥብ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ወደ ጎረቤት ሀገራት እና መካከለኛው ምስራቅ የሚላኩ የአቮካዶ ምርቶችን ጨምሮ እንደአጠቃላይ በክልሉ 12 ሺህ ኩንታል የአቮካዶ ምርት ኤክስፖርት ለማድረግ መታቀዱን ጠቁመዋል ፡፡

ከባለፈው ዓመት ሰኔ ወር ጀምሮ 20 ሚሊዮን የአቮካዶ ችግኝ ለማዘጋጀት ወደ ሥራ ተገብቷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እስከ ታህሳስ ወር 2017 ዓ.ም ድረስ 12 ነጥብ 5 ሚሊዮን ችግኝ ማዘጋጀት መቻሉን አስረድተዋል፡፡

የአቮካዶ ምርታማነትን ለማሳደግ፤ አዳዲስ የአቦካዶ ዝርያዎችን ለማልማት የግብዓት ችግር ማጋጠሙን አመልክተው፤ ችግሩን ለመቅረፍ በክልሉ በሚገኙ 270 ችግኝ ጣቢያዎች በሽታን የሚቋቋሙ፣ ምርታማ እና ገበያ መር የሆኑ ዝርያዎች የማባዛት እና የአቅርቦት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡


በአቫካዶ ልማት በስፋት ማልማት አዲስ እንደመሆኑም የልማት ሠራተኛው ድረስ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ አርሶ አደሮች ከ50 በላይ የአቮካዶ ችግኝ በክላስተር እንዲተክሉ እየተደረገ ነው፡፡ ምርቱ ቶሎ የሚበላሽ እንደመሆኑም አርሶ አደሮችና ላኪዎች በምን አይነት መልኩ ማስቀመጥና መላክ እንዳለባቸው ሥልጠና እየተሰጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ አሁንም ክፍተቱ ሙሉ በሙሉ ስላልተቀረፈ ቀጣይ ሥራዎች እንደሚጠበቁ ጠቁመዋል፡፡

በገበያ ትስስር ረገድም አርሶ አደሮች ምርቱን ካመረቱ በኋላ ገበያ የማፈላለግ ሥራ እንደሚሠሩ አንስተው፤ ይህን ለማስቀረት እየተሠራ መሆኑን ነው የተናገሩት ዳይሬክተሩ፡፡

አርሶ አደሮች እና የአቮካዶ አልሚዎች የአቮካዶ ችግኝ ከተከሉ በኋላ በእንስሳት እንዳይበላ እንዲጠብቁ እና አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያደርጉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች





# የእደ ጥበብ ውጤቶችን በቲክቶክ

**ሰሚራ በርሀ**

መገኛው በእንጨት ሥራና የእደ ጥበብ ውጤቶች ከምትታወቀው ጥንታዊቷ የጅማ ከተማ ነው:: በልጅነቱ የተማረውን የእንጨት ሥራ ውጤቶችን ክህሎት በማዳበር ከሚኖርባት ጅማ ከተማ አልፎ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከኢትዮጵያ አልፎ ደግሞ በሌሎች ሀገራት የሚገኙ ደንበኞችን ማፍራት ችሏል:: ወጣት ላይኔ ለማ ይባላል::

የላይኔ እደ-ጥበብ ሁሉንም አይነት የእንጨት ሥራ ውጤቶች፣ ቅርጻቅርጾች፣ የቤት ውስጥ ማስዋቢያዎችን ይሰራል:: ከሚኖርባት የጅማ ከተማ አልፎ ጊዜው በፈጠረው የቲክ ቶክ ማኅበራዊ ገጽ ላይ የሚሰራቸውን ሥራዎቹን በማስተዋወቅ በርካታ ተከታዮችን በገጹ ላይ አፍርቷል:: ‹‹ ወደ እዚህ ሥራ የገባሁት ከአባቴ ተምሬው ነው:: ጅማ በእንጨት ሥራ ውጤቶች ለረጅም ዘመናት የምታወቅ ከተማ ነች:: ›› የሚለው ወጣት ላይኔ አባቱ ምንም እንኳን የመምህርነት ሙያ ላይ ያገለግሉ የነበረ ቢሆንም የእደ ጥበብ ውጤቶች በልዩነት የተሳቡበት ዘርፍ መሆኑን ያስታውሳል::

አባቱ የተሳቡበትን ይህንን ሙያ ከዋናው የመምህርነት ሥራቸው ባለፈ የእንጨት ሥራዎችን ሲሰሩ ሙያውን ወደ ልጃቸው እንዲተላለፍም ይፈልጉ ነበር:: ላይኔ ይህንን የእደጥበብ ውጤት ከልጅነቱ ጀምሮ በማየቱ መሰረታዊ የሙያውን ክህሎት ሊቀስም ችሏል:: የዚህ ሙያ ባለቤት በመሆኑ የሚኮራው ወጣት ላይኔ ወደ ሥራው ዓለም ሲገባ የራሱን መንገድ ለመፈለግ ረጅም ጊዜ መውሰዱንም ያስታውሳል:: ‹‹ የተለያዩ ሥራዎችን ለመስራት ሞክሬያለሁ ከዚያ በኋላ ነው ይህንን በልጅነቴ የተማርኩትን ወደ ሥራ መለወጥ የቻልኩት፡ ›› ይላል::

‹‹ አንድን ሙያ ለመማር የሚጠይቀው ጊዜ እንደ ሚማረው ሰው ይወሰናል:: ፍላጎት እና ጥረት ያለው ሰው ከሆነ በአጭር ጊዜ ሊማረው ይችላል:: ›› ላይኔ በሥራው ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ከጀመረ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል:: ለረጅም ጊዜ ሲሰራበት የቆየውን ባኅላዊ ጥበብ ከዘመናዊ ጥበብ ጋር በማጣመር ለመማር ያለ ምንም አስተማሪ ወይም ባልተመቻቸ ሁኔታ በራሱ ጥረት መማሩን ገልጿል::

በእንጨት ሥራ ሙያ ውስጥ አብዛኛው ሥራዎችን ለማከናወን ዘመናዊ ማሽኖች ድካምን የሚያቀሉ እና ጊዜን የሚቆጥቡ ዘመናዊ መሳሪያዎች እንደሚገኙ ይገልጻል:: ላይኔ ሥራውን በጀመረበት ወቅት በአካባቢው የሚገኙ ባለሙያዎችን እና የሚፈልጋቸውን አነስተኛ ማሽኖች በመጠቀም እንደሆነ ያስታውሳል:: ‹‹ የምጠቀማቸው ማሽኖች ቢኖሩም አብዛኛውን ሥራ የምሰራው በእጅ ነው:: እነዚህ ማሽኖች በሌላው ዓለም ላይ ተመርተው በቀላሉ የሚገኙ ሲሆን ወደሀገራችን ሲገቡ ግን እንደ ቅንጦት እቃ ይታያሉ :: ከሚገዙበት ከፍተኛ ዋጋ በላይ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚጠየቅባቸው ቀረጥ ከፍተኛ ነው:: የእደጥበብ ሥራዎች ውጤታቸው የእንጨት ሥራዎች ከመሆናቸውም ባለፈ በእጅ የተሰሩ መሆናቸው ዋጋቸውን ከፍ ያደርገዋል:: ነገር ግን ከዋናው የእንጨት ግብዓት የአዕምሮ ፈጠራን ለማሳረፍ ያለቀለት ግብዓት እንዲሆን የሚያግዙ ማሽኖች አስፈላጊነታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም::››ሲል ችግሩን ያስረዳል:: እንደ ላይኔ ገለጻ በእደጥበብ ውጤቶች ዘርፍ የተሰማሩ በርካታ ባለሙያዎች ያሉ ሲሆን ለሌሎች ወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ወደ ዚህ ሥራ እንዲሰማሩ ይህ ክፍተት መታየት ይገባዋል::

ላይኔ በአባቱ አማካኝት የተሳበበት የእንጨት ሙያ ከሚሰራው ሥራ ጎን ለጎን በመስራት ሙያውን ለማዳበር ችሏል:: በሙያው ላይ አምስት ዓመት ያክል ጊዜ ቆይቷል:: ወጣት ላይኔ ኑሮውን ያደረገው በጅማ ከተማ ውስጥ ቆጪ የምትባል ከተማ ውስጥ ነው:: ታዲያ እንጨት ሥራ የእደጥበብ ውጤቶቹን አንድ ደንበኛ ለሌላው ሰው በማስተላለፍ ሲሰራ ከቆየ በኋላ የሙሉ ጊዜ ሥራው በማድረግ በብዙዎች ዘንድ እውቅናን ማግኘት ችሏል::


ወቅቱ ሰዎች ሥራዎቻቸውን በሚሰሩበት ከተማ እና ቦታ ብቻ ተወስነው የሚያደርጉት ሳይሆን በሚኖሩበት ከተማ ሆነው በመላው ዓለም ተደራሽ መሆን የሚችሉበት ነው:: ላይኔም ጊዜው የፈጠረውን የቲክቶክ ማኅበራዊ ገጽ በመጠቀም የራሱን ሥራዎች ይዞ ብቅ ብሏል ::

ማኅበራዊ ገጽ ላይ በእደ ጥበብ ውጤቶች ላይ ሰዎች ያላቸው አቀባበል እምብዛም እንዳልነበር ይገልጻል:: በዚህም በገጹ ላይ ተከታዮችን ለማፍራት፣ ሰዎች ያላቸውን ግንዛቤ ለመቀየር እና ሥራውን ለማስተዋወቅ ሰፊ ጊዜን ወስዶበታል::‹‹በሀገራችን ለእደጥበብ ውጤቶች ያለው ተቀባይነት በሌሎች ሀገራት እንደምንመለከተው አይደለም:: ›› የሚለው ላይኔ በቲክቶክ የማኅበራዊ ገጹ ላይ ሥራውን በማስተዋወቅ የራሱን የፈጠራ ሥራዎች በተለያየ መንገድ በማሳየት የእንጨት ሥራ ውጤቶች በተለያየ መንገድ መሰራት እንደሚችል በማሳየት በርካታ ተከታዮችን አፍርቷል::

በአንድ ወቅት በገጹ ላይ ኢትዮጵያን ካርታ የአንበሳ ምስልን በማድረግ የሰራው ማስዋቢያ ከፍተኛ እይታን ያገኘ ሥራው ነው:: በእንጨት ላይ በመቅረጽ የአንድ ሳምንት ጊዜ ወስዶ የሰራውን ይህንን ሥራን በማኅበራዊ ገጹ ላይ በጨረታ መልክ አቅርቦታል:: ጨረታውንም በሀገረ ካናዳ ኑሮውን ያደረገና የኢትዮጵያ መለያ የሆነውን የቡና ምርት በማስተዋወቅ እና ለገበያ በማቅረብ የሚታወቅ ድርጅት በዚሁ የማኅበራዊ ገጽ አማካኝነት የቀረበውን ጨረታ በ210 ሺህ ኢትዮጵያ ብር ሊያሸንፍ ችሏል::

‹‹ማኅበራዊ ገጽ ላይ ተከታዮችን ማፍራት ከባድ ነበር:: ነገር ግን በሒደት ሥራዬን የወደዱ በርካታ ደንበኞችን አግኝቼበታለሁ:: ›› ላይኔ በዚህ ገጽ አማካኝነት ከሚኖርባት የጅማ ከተማ አልፎ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ደንበኞችን ማፍራት ችሏል:: ‹‹ ማኅበራዊ ሚዲያ ብዙ በጎ ሰዎችን ሥራዬን የሚያበረታቱ ሰዎችን ያገኘሁበት ነው:: ሥራዬን ለሚወዱ ደንበኞችም ከዚሁ ከጅማ ሆኜ እሰራላቸዋለሁ:: ››

የእንጨት ሥራ ውጤቶችን የቤት ውስጥ



ማስዋቢያዎችን በሚሰራበት ወቅት ደንበኞቹ የሚሰራቸውን ሥራዎች በመመልከት እና የራሳቸውን ሀሳብ በማከል የሚያዙ ሲሆን ባለሙያው ላይኔ ደግሞ በሥራቸው ላይ የተሻለውን በማማከር የሚፈልጉትን እደ-ጥበብ ውጤት ይሰራላቸዋል ::

ወጣት ላይኔ በሥራው ላይ አምስት ዓመት ያክል ጊዜን ይቆይ እንጂ የእደ ጥበብ ውጤት ሥራዎች ላይ የሙሉ ጊዜ ሥራውን በማድረግ ትኩረቱን አድርጎ መሥራት ከጀመረ አንድ ዓመት ከመንፈቅ በላይ ሆኖታል:: ያለፉትን ጊዜያት ተቀጥሮ ከሚሰራበት ሥራ ባሻገር ባለው ጊዜ የተለያዩ የእንጨት ሥራ ውጤቶችን ሲሰራ ቆይቷል:: እነዚህ የእንጨት ሥራ ውጤቶች ከእሱ አልፈው በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅነትን ሲያገኙ የሙሉ ጊዜ ሥራው ለማድረግ መወሰኑን ያስታውሳል:: ላይኔ በተለያየ የሥራ ዘርፍ ላይ ለመስራት ፍላጎት ኖሯቸው መስራት ለሚፈልጉ ወጣቶች የውሳኔ ሰው በመሆን እና ካላቸው እውቀት በመነሳት ለዓላማቸው ጠንክረው መስራት እንደሚገባቸው መልዕክቱን ያስተላልፋል ::

‹‹ እኔ ሥራዬን ስጀምረው በዙርያዬ ሥራዬን አይተው የደገፉኝ ሰዎች ነበሩ:: ነገር ግን የሚደግፉኝ ሰዎች ያገኘሁት መስራት በመጀመሬ ሙከራ በማድረጌ ነው ::››

ላይኔ እደ-ጥበብ የሥራው ስያሜ ሲሆን ከሚኖርባት የጅማ ከተማ ባለፈ በፈጠረው የማኅበራዊ ገጽ በርካታ ደንበኞችን ማፍራት ችሏል:: የራሱን የእደ ጥበብ ውጤቶች የሚሸጥበት ቦታ መክፈት የቅርብ ጊዜ እቅዱ ነው:: ወጣት ላይኔ ይህንን ከአባቱ የተረከበውን የእደጥበብ ውጤት በራሱ ጥረት ያዳበረው በመሆኑ ለሌሎች የሚሆን ትምህርትቤት መክፈት ደግሞ የማይቀር የወደፊት ሕልሙ ነው ::

ወጣት ላይኔ በሚሰራበት የሥራ ዘርፍ በስሩ ለሌሎች ወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል :: ከትምህርት ባሻገር የተለያዩ የሙያ ክህሎት ባለቤት መሆን ጠቃሚ መሆኑንም ጠቅሷል ::



‹‹ወጣቶች ይህንን የሥራ ዘርፍ እንዲማሩት እፈልጋለሁ:: በመሆኑም የመስሪያ እና የመማርያ ቦታ መሆን የሚችል፤ ሙያውን የሚወዱ ሰዎች መሰልጠን የሚችሉበትን የእደጥበብ ትምህርት ቤት መገንባት እፈልጋለሁ :: ››

# የምድር በረከት

# ባሕላዊ ማዕድን አውጪዎችን የመደገፍ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**



የማዕድን ልማት ፋይዳው ብዙ ነው።ሀገር ከዘርፉ የውጭ ምንዛሬ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችንና የመሳሰሉትን እንድታገኝ ያስችላል፤ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች እና ባህላዊ አምራቾች፣ ለማዕድን አዘዋዋሪዎች የገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ይታወቃል።በዓለም ከ50 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ መሰማራታቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።እነዚህ ሰዎች የማዕድን ሥራ የገቢ ምንጫቸው ነው፤ በዚህ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ያስተዳድራሉ።ማዕድን በማውጣት ሥራው የሚያገኙት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ግን እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በኢትዮጵያም ቁጥሩ በውል አይታወቅም እንጂ በጣም በርካታ ዜጎች በባሕላዊ ማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። እነዚህ ሰዎች ማዕድን በማውጣት ሥራ የሚተዳደሩ ቢሆኑም፣ ማግኘት የሚገባቸው ጥቅም ሳያገኙ፤ ሀገርም እንደ ሀገር ማግኘት ያለባትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሳታገኝ ቆይተዋል። ባሕላዊ ማዕድን ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ቀጣይነት ያላቸው ሥራዎች መስራት እንዳለባቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ።

ባለፈው ሕዳር የማዕድን ሚኒስቴር ባዘጋጀው ሦስተኛው የማዕድን ኤክስፖ ላይ ባሕላዊ የማዕድን አምራቾችን የተመለከተ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቧል። በጥናታዊ ጽሁፉ ባሕላዊ ማዕድን የማውጣት ሥራ በኢትዮጵያና በዓለም ያለበት ሁኔታም ተዳሷል፤ የመፍትሔ ምክረ ሀሳብም ቀርቦበታል።

ጥናታዊ ጽሁፉን ያቀረቡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክ ጂኦሎጂስት ፕሮፌሰር ወራሽ ጌታነህ ናቸው። እሳቸው እንዳሉት፤ ጥናታዊ ጽሁፉ በኢትዮጵያ ባሕላዊ ማዕድን አውጪዎች ያሉበት ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል። ጥናቱ ከሌሎች ዓለም አገራት ጋር በማነጻጸር አሁን ያለበት ደረጃ ያሳያል። ለዓለም፣ ለሀገር፣ ለአካባቢ፣ ለማኅበረሰብ እንዲሁም ከግለሰብ እስከ ቤተሰብ ድረስ ያለውን የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ቃኝቷል።

ባሕላዊ የማዕድን ማውጣት ሥራው በዝቅተኛ የሰው ኃይል፣ በአነስተኛ እውቀት እና በግለሰብ ደረጃ የሚሰራ ነው። ይህ ደግሞ ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ድረስ ያለውን ኢኮኖሚ እንዴት ሊደግፍ ይችላል? እንዴትስ እድገት ያመጣል? የሚለው የዓለም አገራት ተሞክሮን ከኢትዮጵያ ጋር በማነጻጸር ዳሰሳ የተደረገበት እንደሆነ ያመላክታሉ።

በጥናቱ እንደተመላከተው፤ ባሕላዊ ማዕድን የማውጣት ሥራው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው። የመጀመሪያው በዘርፉ የተሰማሩ በርካታ ሰዎች መኖራቸው ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖር ያደርገዋል። በዓለም በባሕላዊ ማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ በቀጥታ የተሰማራው ቁጥር 50 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። ይህ ሲባል ደግሞ ለአብነት አንድ ሰው አምስት የቤተሰብ አባላት አሉት ብለን ብንወስድ አምስት በሃምሳ ሲባዛ በዚህ ላይ ኑሮአቸው የተመሠረተው 250 ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎች አሉ እንደማለት ነው። ይህ ደግሞ ትልቅ የኢኮኖሚ አንድምታ ያለው ነው ሲሉ ያስረዳሉ ።

ባሕላዊ ማዕድን ማውጣት ሲባል ማዕድን የሚያወጡትን ብቻ የሚያጠቃልል አይደለም፤ ለማዕድን አውጪዎቹ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ሰዎችም ስላሉ ሌላ ተያያዥ የሆነ ቢዝነስ የሚፈጥር መሆኑን እንደሚያመላክት ይገልጻሉ።ለአብነት ሲጠቅሱ የትራንስፖርት፣ የምግብ፣ የማደሪያ (መጠለያ) አገልግሎት የሚሰጡ እንዲሁም የማዕድን ማውጫ እቃዎችን መሰል አገልግሎቶችን የሚሰጡ በርካቶች መሆናቸው ጠቅሰው፣ ከእነዚህ ጋር ትስስር ያለው ሌላ ኢኮኖሚ ይፈጥራል ሲሉ ያስረዳሉ።

ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት፤በኢትዮጵያ በባሕላዊ ማዕድን ማምረት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ብዛት ትክክለኛ አሀዝ ባይታወቅም፣ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሰዎች በዚህ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል ተብሎ ይገመታል። ይህ ሲባል ቤተሰባቸውን ጨምሮ በዚህ ላይ ኑሮአቸው የተመሰረተ ከአምስት እስከ 7 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች አሉ እንደማለት ነው። በዚህ ቢዝነስ ዙሪያ የተሰማሩና ሌሎች አካላት ሲደመሩ ደግሞ ከ10 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ኢኮኖሚው በዚህ ላይ የተመሠረተ መሆኑን መረዳት ይቻላል።እንደ ኢትዮጵያ 10 ሚሊዮን ሕዝብ ማለት 10 እስከ 15 በመቶ ሕዝብ ኑሮውን በዚህ ላይ አድርጓል ማለት ነው፡፡

ለአካባቢው እድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆን ደግሞ ሁለተኛው ጠቀሜታው ነው።የማዕድን ሥራ መጀመሩን ተከትሎ ብዙ ጊዜ የመሠረተ ልማቶች ይሰራሉ፤ ጥርጊያ መንገድ ይሰራል፤ ይህን ተከትሎም መኪና ይገባል፤ መንደርም ይመሠረታል፤ መንደሩ ወደ ከተማ ያድጋል።

አሁን በኢትዮጵያ የሚታየው ጅማሮ ይህንን ያመለክታል።በአገሪቱ የማዕድን ማውጣት ሥራን ምክንያት አድርገው የተቆረቆሩና የተገነቡ በርካታ ከተሞች እንዳሉም ይገልጻሉ።ይህም የአካባቢው የቢዝነስ እንቅስቃሴ እንዲበዛ እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ ገበያውን ብለው ከተለያዩ አካባቢ ሰዎች እንደሚመጡም አመልክተው፣ ይህም በአካባቢ ልማት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ሦስተኛውና ትልቁ ጠቀሜታው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በማድረግ ማዕድንን ለውጭ ገበያ ማቅረብ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ላላባቸው ማእድን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ነው።ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ወርቅ ትልቅ ድርሻ እንዳለው አመልክተው፣ አሁን ላይ ደግሞ የጌጣጌጥ ማእድናት፣ ታንታለም የመሳሰሉት ማዕድናት ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ እየተገኘ ነው፡፡

እንደሚታወቀው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለውጭ ገበያ ቀርበው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ከሚታወቁ ምርቶች መካከል ከቡናና ከቅባት እህሎች ቀጥሎ ማዕድን ይጠቀስ ነበር። አሁን የማዕድኑ ዘርፍ ቀዳሚ መሆን ጀምሯል፤ በደንብ ማልማትና ማስተዳደር ከተቻለ በቀጣይም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የውጭ ምንዛሪ ችግር ለመቅረፍ ይጠቅማል። የውጭ ምንዛሪ በአንድ አገር ማክሮ ኢኮኖሚ ላይ ምን አይነት ለውጥ እንደሚያመጣ ይታወቃል፤ ማዕድን በዚህ መልኩ ጥቅም ያመጣል የሚል ዓለም አቀፋዊም ሆነ ሀገራዊ እውነታ ላይ የተመሰረቱ ትንታኔዎች እንዳሉም ያመላክታሉ።

እንደ ታዳጊ ሀገር በኢትዮጵያ በባሕላዊ ማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ብዙ ችግሮች ይታያሉ የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ የመጀመሪያው የሕግ ማሕቀፍ ችግር እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ሲባል ሕግ የለም ማለት ሳይሆን ሕጉ በአንድ አይነት ሁኔታ በሁሉም አካባቢዎች አይተገበርም ሲሉ ያብራራሉ። ይህም ሕገወጥ የማዕድን ማውጣት ሥራና ግብይት እንዲኖር ያደርጋል ይላሉ።

ሕግ ሥራ ላይ ካልዋለ የማዕድኑ ምርት ታክስ እንደማይደረግ ተናግረው፣ ሕግ የግድ ሥራ ላይ ካልዋለ ማዕድኑ ከሕገ ውጪ በሆነ ሁኔታ ወደ ውጭ የሚወጣባቸው መንገዶች ይበዛሉ ብለዋል።እሳቸው እንዳብራሩት፤ የኢትዮጵያ ወርቅ እና ሌሎች ማዕድናት ሕገወጥ በሆነ መንገድ በድንበር እንደሚወጡ ይነገራል። በዚህም ሕገወጦች ይጠቀሙበታል፤ መንግሥትና የአገሪቱ ዜጎች አይጠቀሙበትም። ሕገወጥ የማዕድን ዝውውር አለ ማለት እንደ ሀገር ማግኘት የሚቻለውን በርካታ ጠቀሜታ ያሳጣል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሕግ ሥራ ላይ እንዳይውል የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች እንዳሉም ጠቁመዋል።ሕግ ሥራ ላይ እንዳይውል ከሚያደርጉት መካከል የመጀመሪያው ሰላምና መረጋጋት አለመኖር ነው።እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች በተለይ በማዕድን ማውጫ አካባቢዎች ላይ መረጋጋት ሳይኖር ሲቀር ሕጉን ለመተግበር እንደሚያስቸግር ይገልጻሉ፡፡

ሌላው ችግር በማዕድን ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የእውቀት ክፍተት መሆኑን ገልጸው፣ ማዕድን እንዴት ይወጣል? እሴት እንዴት ይጨመራል ስለሚሉትና ስለማዕድን ቢዝነስም ጥልቅ እውቀት ያላቸው ባለመሆናቸው፣ የሚያገኙትን ገንዘብ እንዴት አድርገው ወደሚያዋጣ ቢዝነስ መቀየር እንዳለባቸው እንደማያውቁ ተናግረዋል፤ በዚህ የተነሳም የሚያገኙትን ገንዘብ ወደ ሀብትነት ሳይቀየሩ እንደሚባክንባቸው ያስረዳሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ እውቀቱ ቢኖራቸው ግን ገንዘቡን ሌላ ቦታ ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ፤ እንደገናም ቋሚ ነገሮች ላይ እንዲውል ቋሚ የገቢ ምንጭ በመቀየር መጠቀም ይችሉ ነበር። ማዕድን ተሸጦ የሚገኝ ገንዘብ እንዲባክን አያደርጉም። አንዳንድ ማዕድን የሚወጣባቸው ቦታዎች በጣም ሩቅ መሆናቸውም ሌላው ገንዘቡን የሚያስቀምጡባቸው ባንኮች ላያገኙ ይችላሉ፤ ይህ ችግር ባንኮችም እየተስፋፉ መምጣታቸውን ተከትሎ እየተፈታ ይገኛል።

ባሕላዊ የማዕድን አውጪዎች ገንዘብ (ካፒታል/የላቸውም የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ ማንኛውንም ሥራ መነሻ ካፒታል እንደሚያስፈልገው ሁሉ ማዕድን የማውጣቱ ሥራም ካፒታል እንደሚጠይቅ ይናገራሉ። መነሻ ካፒታል የሌላቸው በርካታ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ አንዳንዶቹ አካፋና ዶማ መግዛት የማይችሉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ ፕሮፌሰሩ ማብራሪያ፤ የገበያ ችግርም ይስተዋላል። ብዙ ጊዜ ማዕድን አውጭዎች ከምርታቸው ተገቢውን ጥቅም አያገኙም። ከእነሱ ይልቅ ደላሎች አልያም ሕገወጦች ናቸው የሚጠቀሙት። አውጪዎቹ ስለገበያው አያውቁም፤ ምናልባትም አንድ ሚሊዮን ብር የሚሸጥ አንድ የጌጣጌጥ ማዕድን በሃምሳና በመቶ ሺ ብር ሊሸጡት ይችላሉ። ይሄ በገሃድ የሚታይ ሀቅ ነው። አንዳንዶቹ ድንጋይ ይህንን ያህል ሃምሳ ሺ ብር ካወጣ ምን ያስፈልጋል እስከማለት ይደርሳሉ።አለማወቃቸው እንጂ ያ ማዕድን በሚሊዮን ብር ሊሸጥ የሚችል ነው። ይሄ ከገበያ መረጃ አለመኖር ሊመነጭ የሚችል ችግር ነው፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ የገበያ መረጃ አለመኖር ብቻ ሳይሆን የገበያ አቅርቦቱም በራሱ ሌላኛው ችግር ነው። ማዕድናቱን ገበያ አውጥተው የሚገዛቸው ካጡ በማይረባ ዋጋ ይሸጡታል። በተለይ በገጠር ገበያዎች በተለምዶ እንደሚባለው ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ሁሉም ነገር ይረከሳል፤ ምክንያቱም ሻጩ ወደ ገበያ ይዞ የወጣውን ወደ ቤቱ ከሚመለስ ባገኘው ዋጋ ሸጦ መመለስን ይመርጣል፤ የማዕድን አውጪዎች ችግር ይሄ ነው። ደላሎቹ ደግሞ የሚገዛቸውና አማራጭ ሲያጡ በርካሽ ዋጋ ይሸጣሉ በሚል አውቀው ዝም ይሏቸዋል" ሲሉ ፕሮፌሰሩ ይገልጻሉ። ይህም የአካባቢውን ሕዝብ እየጎዳ ያለ ትልቅ ችግር መሆኑን ጠቅሰው፤ ዜጎችና ሀገር ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ሀብት የሕገወጦች ሲሳይ እንዲሆን እያደረገ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ባሕላዊ የማዕድን አውጪዎች ከማዕድን ዘርፉ ተጠቃሚ ሆነው ሀገርንም እንዲጠቅሙ ለማድረግ መፍትሔው የሚደረገው ድጋፍና ክትትል አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሆነም ፕሮፌሰሩ ያመላክታሉ።"በሰው ልጅ ታሪክ መንግሥት ያስፈልለገበት ዋንኛው ምክንያቶች ሰላምና ጸጥታ ለማስከበርና የጋራ ሀብትን ለማስተዳዳር ነው፤ ይህ ደግሞ መንግሥት ለአንድ ሀገርና ሕዝብ ሊያደርገው የሚገባ ነው » ይላሉ

እሳቸው እንደሚሉት፤ ችግሩን የመፍታቱ ሥራ መጀመሪያ ሕግና ሥርዓትን መዘርጋትና ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግን ይጠይቃል። ሁለተኛ ዘርፉ ለአገር ካለው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንጻር እየታየ ለአምራቾቹ አስፈላጊው ድጋፍ መደረግ አለበት። ባሕላዊ ማዕድን አውጪዎች የገንዘብ አቅም ሆነ እውቀት ስሌላቸው በተደራጀ መልኩ ድጋፍ ሊደርግላቸው ይገባል። ይህ ሥራ ለመንግሥት ብቻ የሚተው አይደለም፤ የግል ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት ለማዕድን አውጪዎች ድጋፍ ቢያደርጉ እነርሱም በቀላሉ ከደህነት ይወጣሉ፤ ሀገርንም ይጠቅማሉ። የሕግ የበላይነትን ማስፈን እና ድጋፍ ማድረግ ብዙ ችግሮች ይቀርፋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የእሳት ዳር ወግ

ሀብታሙ ባንታየሁ

ከእድሜ ዘለላ ቅጥያ ከነፍስ ህላዌ ምስያ የሃቅ ስሜት ያፋፋት ሰሞነኛ የብእር ቱርፋት መቆያ እንዲሆነን ከወግ ሰበዝ ይህን ልምዘዝ፡፡

አው አለ ጅብ ... ሰማኸው? ትናንት አማኸው? ኧረ ቆይ... ጅብ ሲጮህ አፋን ከመሬት የሚተክለው ለምንድነው? የእግዜር ዙፋን እንዳይነቃነቅ፣ ጨረቃ እንዳትጠልቅ፣ ፀሐይ እንዳትወድቅ መሰለኝ፤ ለነገሩ በፈጣሪ የተገባለትን ቃል ማስታወሱም ሊሆን ይችላል፡፡ የምን ቃል አትሉኝም? በእኔ መጀን መልሱ ይሄውላችሁ፡፡

ለዳግም ምጽአት ምልክት ከሆኑት ውስጥ የጅብ በቀን መውጣት አንዱ እንደሆነ መቼም አይጠፋችሁም፡፡ ሁለት ፀጉር ያበቀሉ ሰዎች ሲያስረዱ “በስምንተኛው ሺ የጅብ መፍራት፣ ይሉንታ ማጣት ነውርነቱ ይቀራል” ይላሉ፡፡

በድሮ ጊዜ “ከአይጥ ቤት ብቅል ከድመት ቤት ቋንጣ” ሳይታጣ በፊት ጅብ አህያን ይፈራት ነበር አሉ፡፡ ኋላ አንድ ቀን የጅብ ልጅ ይሞትና አህይት ወገኖቿን ሰብስባ ለቅሶ እንደመጣች ለእዝን ከያዙት ድርቆሽ ያቀርብላቸውና አያ ጅቦ ከፊታቸው ተገመረ፡፡ የአህያን አበላል አይቶ ጎመጀና ምራቁን ሲውጥ ገርገጭ የሚለው ድምጽ ጆሮዋን ከጣለችበት ቅርጫት አህያን ቀና አደረጋት፡፡ “ምነው አያ ጅቦ” አለች በድንጋጤ የጎረሰችውን እንኳን ሳትውጥ፡፡

“አበላልሽ አስቀንቶኝ ረሃቤን ቀሰቀሰውና ምግብ አሰኝቶኝ አብሬሽ ልበላ ነበር ግን...” ብሎ ሃሳቡን በእንጥልጥል ተወው፡፡ “ግን ምን?” አለች አህያ እንደመሽኮርመምእየቃጣት፡፡አያጅቦቀንዷ እንዳይወጋው መስጋቱን ቢነግራት አህያ በሳቅ እየተንፈራፈረች ቀንዷ ሳይሆን ጆሮዋ መሆኑን ገለጠችለት፡፡ ከዚያን እለት ጀምሮ “ላታመልጪኝ አታሩጪኝ” በሚለው የተፈጥሮ ሕግ አያ ጅቦ መፍራቱን አህያ ለቅሶ መድረሱንም በይፋ ሻሩት፡፡ ፍርሃት ብትሉትስ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡

የአባትሽን አጥር ጅብ የፈራውን፣
ሲዞረው አደረ ልቤ ብቻውን፡፡

ስል የዘፈንኩላት ሥልጣኔን ያሻረችኝ፣ ትጥቄን ያስፈታችኝ ስፍራሽ የምትባል ጎረቤቴ ነበረችና ከመንደራችን ድድ ማስጫ ተቀምጬ አላፊ አግዳሚው በአይኔ ስመዝን ሰቀቀን የሆነችብኝ ደማም ብቅ አለች፡፡ እርግማኗ ምርቃት ስድቧ ሙገሳ ስለሚመስለኝ ምነው ቆንጂት በቀን ጅብ ይወጣል እንዴ? ብላት “አዎ አንዳንተ አይነቱን አህያ ሊበላ ይወጣል” አለችና ረግጣኝ አለፈች፡፡ እነተረት አያልቅበት ...

“የመውደድ ነገር ቢሰማ ጅብ፣
ልጆቹን ይዞ አጀብ አጀብ፡፡”

ብለው የገጠሙት እሷን አይተው መሆን አለበት፡፡

የጅብ መውደድ ከተነሳ አይቀር የእድራችን ጥሩንባ ነፊ አያ ሸንቁጤን የጉለሌው ሰካራምን ያነበቡ ሰዎች “አክትፍ አበጀን ነው” ይሉታል፡፡ በጎመጁ ጠጅ ቤት የሚያውቁትና የብርሌ አንገት የሚያጫብጡት ወዳጆቹ የሰዓቱን መግፋት አይተው “ቤትህ ጅብ ዋሻን አልፎ አይደለም? መሽቷልኮ” ሲሉት በሶስት ብር የፍየል ጭንቅላት ገዝቶ በመጋበዝ ያላመደውን ጅብ እየተመካበት “ሸኚ አለኝ” ይላቸዋል በኩራት፡፡

ግሪኮችም እንደ አያ ሸንቁጤ ሀተታ ተፈጥሯቸውን (ሚቶሎጂያቸውን) ሁሉ ለጅብ በመስጠት መልካም እሴቶቻቸውን ለመገንባት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። እኛ ግን በተቃራኒው ለልጆቻችን ማስፈራሪያና ለእኩይ ድርጊት ምሳሌ አድርገነዋል፡፡ በሥራ ላይ የማይለግምን ሰው ሲሠራ አቅሙ የጅብ ነው ብለን ያደነቅነውን ያህል “የሠራ ይብላ” የሚለውን ቅዱስ ቃል ሽረን አበላሉ እንደ ጅብ ነው በማለት የሆዳምነት መልክ ኳልነው፡፡

ለዚህ ሃሳብ ማሳያ ይሆነኝ ዘንድ አንድ ጽሁፍ ዋቢ መጥቀሱ ነገሬን ያደምቀዋል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም “አዳፍኔ” መጽሐፋቸው ላይ “ጅብን መጥራት” በሚል ርእስ ያሰፈሩት ትዝብት ይህን ይመስላል፡፡ ሸዋ በሄዱበት አጋጣሚ የበሬን ግንባር የምታክል የአንድን አርሶአደር ማሳ ሲጎበኙ አንጀታቸው ተላውሶ “ሌላ የለህም?” ሲሉ ጠየቁት፡፡ “አለኝ ግን ጅብ ስለሚጠራብኝ አላርሰውም” አላቸው ፊቱን በኀዘን ቅጭም አድርጎ፡፡ ማን ያውቃል ... አውደ ነገሥትን ሲገልጡ በገውዝ ንፋስ ኮከብ ስር የሰፈረውን “እንደ ጅብ ሳይበላ አያድርም” የሚለውን አንብበው ይሆናል፡፡ ትርጉሙን አንሻፈውት እንጂ በየደረሰበት ሥራ ይሳካለታል ማለቱ ነበር፡፡

ግን ጅብ ለምን ፈሪ ሆነ? አንድ ቀን ብርሃን ለጭለማ ቦታውን ሲለቅ እቁባቱ ናፍቃው ወደ ከተማ ከሚገሰግስ ሽፍታ ጋር ተገጣጠመና ሴት ዘንድ እንደሚሄድ ልቦናው ነግሮት አያ ጅቦ በቅናት እምሽክ አደረገው፡፡ ይመጣል ብላ ተሰናድታ ስትጠብቅ ውሽማዋ ቀርቶ እርር ኩምትር ያለችው ወ/ሮ ስትበጥስና ስትቀጥል ያደረችውን እንዝርት አሸቀንጥራ ንጋቱ የአህያ ሆድ ሲመስል እንስራዋን አንጠልጥላ ወንዝ ስትወርድ ገላዋ የተራበው ወንድ እንዳይሆኑት ሆኗል። ምንም እንኳን ኀዘኗ ከብዶ ብታነባም የቀረ አካሉን ከማንሳት ይልቅ የጅብ አስራ ማሪያምን ታሪክ ታውቃለችና ለበቀል ጥርሷን ነክሳ ተመለሰች፡፡

ከበሮው የተሠራበት ቆዳ ያልደረቀ በመሆኑ ይሸተውና ርሃቡን ለማስታገስ እየጎተተ ሲወጣ በሩን ማለፍ አልቻለም፤ ይህን ያዩ ካህናትም “ጅብ አስራ ማሪያም” ሲሉ ደብሩን ሰየሙት፡፡

ለአስተርዮ ማሪያም ያኖረችውን ብቅል ከተሰቀለበት አውርዳ ከሥፍራው ስትደርስ በተቀዳደደ ልብሱ ግራ እጁንና ግራ እግሩን ከፍና ብቅሉን ሰባት ጊዜ ብታዞርበት አያ ጅቦን ለተጨማሪ ግዝት ዳረገችው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጅብ በሕይወት ያለን ሰው ይቅርና አስከሬን ቢሆንም ሰባት ጊዜ ዞሮ (አሽትቶ) ካላረጋገጠ በቀር ለመብላት አይደፍርም፡፡

ሊሆን ይችላል ብዬ በማሰብ ጅብ አውድማ ውስጥ ለምን እንደማይገባ ምክንያቱን እንድትነግረኝ አያቴን ጠየኳት፡፡ ያሲያዘችኝን የዶሮ አይን የመሰለ ጠላ እየኮመኮምኩና ያቀረበችልኝን ሰነፍ ቆሎ እያንቀራጨሁ ያስለመድችኝን የእሳት ዳር ወግ ከስሩ ስታስጨብጠኝ ለመቅለብ እዝነ ልቦናዬን አሰላሁ፡፡ “አጉማስ ሲጣል ድግሱ ማለፍያ ነውና ጠላ እስከ ተሾመ ድረስ የማሪያም ብቅል ግዝት አያ ጅቦን “ማህረቤን ያያችሁን” ያዙረዋል እንጂ አውድማው ውስጥ ለመግባት አያሰናዝረውም” አለች ከያዘችው ዋንጫ ጠላ ጎሮሮዋን ለማርጠብ እየተጎነጨች፡፡

ቀጠለችና “አባሲኖዳን ታውቃቸዋለህ? ስትል ጠየቀችኝ፡፡ ፍቅር እስከ መቃብርን ማንበቤን ገልጬ በዛብህ ያስተማረበት ደብር መሆኑን ነገርኳት ከጨዋታችን ጋር ምን እንደሚያገናኘው ለመስማት ጓጉቼ፡፡ አያቴ ሙሉ ጎጃም ፍቅር እስከ መቃብርን አንብባዋለች ሳይሆን ኖራዋለች ነው የሚባለው፡፡ “ልክ ብለሃል” አለችና የደብተራ ቀለመ ወርቅንና የበዛብህን ዳና ተከትላ “የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል”፣ “ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል” የሚሉት ተረትና ምሳሌዎች የበቀሉበትን የአባሲኖዳን ደብር ልታስጎበኘኝ የብራና መዛግብትን ገለጠች፡፡

“አንዲት መነኩሴ የአባሲኖዳን ጸበል የያዙበት ቅል ከእጃቸው አፈትልኮ ድንጋይ ላይ በወደቀ ጊዜ ቅሉ ሳይሆን ድንጋዩ ለሁለት ተከፈለ፤ ይህን ታምር ያዩ ሁሉ “ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል” ሲሉ ተረቱ፡፡ አንድ ቀን እንደዚሁ ለአባሲኖዳ በስለት የገባውን ሙክት አንድ የተራበ ጅብ ሲከመርበት የሾለ ቀንዱ በጎሮሮው ተሰነቀረና ሞተ፤ “የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል” የሚለው አባባልም መነሻው ይህ ሁነት ነው ይላሉ” ብላ ትንፋሽ ለመውሰድ ወሬዋን ገታች፡፡ “በድሮ ጊዜ” እያለች ያየችውንም የሰማችውንም ስታወጋኝ የቃምኩትን ቆሎ ሳልውጥና ቆሎ ያቀረበችበትን ገበታ እንደያስኩ ከምድጃው ስር እንቅልፍ ይጥለኛል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የትራምፕ አስተዳደር የዩክሬን ልዩ መልዕክተኛ በሩሲያ ጉብኝት ሊያደርጉ ነው

የፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የዩክሬን እና የሩሲያ ልዩ መልዕክተኛ ኪት ኬሎግ በሚቀጥለው ወር ኪቭን ከጎበኙ በኋላ ወደ ሞስኮ ለመጓዝ ማቀዳቸውን ብሉምበርግ ጉዳዩን የሚያውቅ ምንጭ በመጥቀስ ዘግቧል። ምንም እንኳን እቅዱ በውሳኔ ደረጃ ባይጎለብትም ኬሎግ ወደ ሩሲያ የሚያቀኑ ከሆነ የተለየ ፖሊሲ ማስተግበር ላይ ከማተኮር ይልቅ በሞስኮ በኩል የሚነሱ ሃሳቦችን መረጃ በማሰባሰብ ላይ ሊያተኩሩ እንደሚችል ተገልጿል፡፡

ልዩ መልዕክተኛው ወደ ምስራቅ አውሮፓ ከመጓዛቸው በፊት ወደ ለንደን ፣ ፓሪስ እና ሮም በማቅናት በአካባቢው ሁኔታ ዙርያ ከከፍተኛ አመራሮች ጋር እንደሚመክሩ ይጠበቃል፡፡ በመጀመሪያው የትራምፕ የሥልጣን ዘመን በብሔራዊ ደህንነት ሚናዎች ላይ ያገለገሉት ጡረተኛው ጄኔራል፤ በሞስኮ እና በኪየቭ መካከል የሰላም ስምምነትን ለማደራደር በመሞከር የወደፊቱ አስተዳደር ቁልፍ ሰው ሆኖው ባለፈው ወር ተሹመዋል፡፡

በብሉምበርግ ዘገባ መሠረት ኬሎግ እና ሌላው የቀድሞ የትራምፕ አማካሪ ፍሬድ ፍሊትዝ ሩሲያ ለተቆጣጠረቻቸው ቦታዎች እውቅና ሳይሰጥ አሁን ባለበት ሁኔታ ግጭቱ እንዲቆም የድርድር ሃሳብ ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባሉ ተብሎ



ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ባለፈም ሁለቱ በዩክሬን ሩሲያ ጦርነት ዙርያ በቅርበት እየሠሩ የሚገኙ አካላት ጦርነቱን በዘላቂነት ለማስቆም የዩክሬንን የኔቶ አባልነት ጥያቄ ለረጅም ጊዜ ማዘግየት እንደሚገባ ምክራቸውን መለገሳቸው ተሰምቷል፡፡

በምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅት ጦርነቱን በ24 ሰአት አስቆማለሁ ሲሉ የተደመጡት ትራምፕ ለዩክሬን የሚደረግ ወታደራዊ ድጋፍን በመያዣነት በማቅረብ ኪየቭ ወደ ድርድሩ እንድትቀርብ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችል የዲፕሎማሲ ተንታኞች ያነሳሉ፡፡

የፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የዩክሬን እና የሩሲያ ልዩ መልዕክተኛ ኪት ኬሎግ ተመራጩ ፕሬዚዳንት ደም አፋሳሹን ጦርነት ሊያስቆሙ እንደሚችሉ፤ ፕሬዚዳንት ፑቲን እና የዩክሬኑ አቻቸውን ዘለንስኪን በበዓለ ሲመታቸው ላይ እንዲታደሙ ግብዣ ሊያቀርቡ እንደሚችሉም ተናግረዋል፡፡ ትራምፕ እራሳቸው ጦርነቱን በማስቆም ዙርያ ከዘለንስኪ እና ፑቲን ጋር ለመነጋገር ዝግጁ መሆናቸውን መናገራቸው መዘገቡ ይታወሳል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ፑቲን ተመራጩ ፕሬዚዳንት የዩክሬንን ግጭት በማስቆም ላይ የሰጡት መግለጫ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን በመጥቀስ ትራምፕን ለማነጋገርም ሆነ አስቀድመው ስልክ ለመደወል እንደማይከብዳቸው ተናግረዋል። ነገር ግን ዩክሬን በዘላቂነት የኔቶ አባል እንደማትሆን ማረጋገጫ ማግኘት እና ሩሲያ አሁን የተቆጣጠረቻቸውን ክልሎች እውቅና እንዲሰጥ ክሪምሊን ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ አሁንም አልቀየረም፡፡ ፕሬዚዳንት ፑቲን እና የዩክሬኑ አቻቸው በትራምፕ በዓለ ሲመት ላይ እንዲታደሙ ሊጋበዙ እንደሚችሉም ተነግሯል ሲል አል ዐይን ዘግቧል፡፡


## ዶሮ በመስረቁ ለ10 ዓመታት የታሰረው ናይጄሪያዊ ይቅርታ ሊደረግለት ነው

ዶሮና እንቁላል በመስረቁ ለ10 ዓመታት ታስሮ የሞት ቅጣት ሲጠባበቅ የነበረው ናይጀሪያዊ ይቅርታ ሊደረግለት እንደሚችል ተገለጸ። የናይጀሪያ ደቡብ ምዕራብ ግዛት ኦሳን ሀገረ ገዢ ይቅርታ ለማድረግ ቃል እንደገቡለት ተገልጿል። እአአ በ2010 ሴጉን ኦሎዋከሬ የ17 ዓመት ወጣት ሳለ በስርቆት የታሰረው በድርጊቱ ተሳትፏል ከተባለው ሞራክዩ ሰንደይ ጋር ነበር። የፖሊስ ኃላፊ ቤት ላይ ጥቃት አድርሰዋል ተብለዋል። ሌላንም ሰው ከእንጨት በተሠራ ሽጉጥ በማስፈራራት ዶሮና እንቁላል ሰርቀዋል።

በ2014 የኦሱን ግዛት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ጂድ ፋሎላ ሁለቱንም ታንቀው እንዲሞቱ ፈርደውባቸዋል። የፖሊስ ኃላፊ ቤት በመዝረፍ ጥፋተኛ ተብለዋል። የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በጣም የከፋ ነው በሚል ከሕዝቡ ቅሬታ ተሰምቷል። ሁለቱም እስረኞች ሌጎስ ወደሚገኘውና ከፍተኛ ጥበቃ ወደሚደረግለት ኪሪኪሪ ማረሚያ ቤት ተወስደው የሞት ፍርድ እየተጠባበቁ ነበር።

ሀገረ ገዢው አድሞላ አድሌኬ የሰው ሕይወት ዋጋ ስላለው ለ10 ዓመታት የሞት ቅጣት ሲጠባበቅ የነበረው ሴጉን ኦሎዋከሬ ይቅርታ ሊደረግለት ይገባል ብለዋል። “የፍትሕ ሚኒስትር ለዚህ ወጣት የይቅርታ ሂደት እንዲጀምሩ ትዕዛዝ ሰጥቻለሁ። ኦሱን የፍትሕና እኩልነት ግዛት ነው። ፍትሐዊነትንና የሕይወት ዋጋን ማክበር አለብን” ብለዋል።

ሌላኛው በእስር ላይ ያለው ሞራክዩ ሰንደይ እጣ ፈንታ ምን እንደሆነ እስካሁን የተባለ ነገር የለም። ይቅርታ ይደረግለታል የተባለው ሴጉን ኦሎዋከሬ ቤተሰቦችና የሠብዓዊ መብት ተሟጋቾች ለዓመታት ከእስር እንዲለቀቅ ሲጠይቁ ነበር። ብቸኛ ልጃቸው እንዲለቀቅ እያለቀሱ ወላጆቹ ሲጠይቁ በቅርቡ በአንድ ፖድካስት ላይ




ተደምጠዋል። በ2025 ይለቀቃል ተብሎም ይጠበቃል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

ሀገርኛ

# ሦስት ሀገራትን ያስተሳሰረው -ሔር ኢሴ

ቤዛ እሸቱ



አባቶች በብሔሩ አጠራር ገንዴዎች በተራራው ላይ ክብ ሰርተው ምክክር ሲያደርጉ፤

የሰው ልጅ ሰብሰብ ብሎ ሲኖር ግጭት ርቆት ሰላም ይቀርበው ዘንድ ሕግ ማውጣቱ የተለመደ ነው:: ችግሩ የሚወጡት ሕጎች በተለያየ ምክንያቶች ጊዜ በሄደ ቁጥር የመከበር እድላቸው እየቀነሰ በአዲስ ሕግ ይተካሉ:: በተለይ ካልተጻፉ የመረሳት እድላቸው ሰፊ ነው:: የሱማሌ ብሔር አካል የሆኑት የኢሳ ማኅበረሰቦች ሕግ አለመጻፉም ሆነ ጊዜው መርዘሙ በሕጋቸው ላይ ለውጥ አላመጣም::

ኢሳዎች "ሔር ኢሴ" ሲሉ የሚጠሩት ሕጋቸው ከወጣ 500 ዓመታትን ቢሻገርም ማኅበረሰቡ አሁንም ይተገብረዋል:: ሔር ሕግ ማለት ሲሆን ኢሴ የኢሳዎች መሆኑን ለማመላከት የገባ ነው:: በሔር ኢሳ አሁንም ፍትህ ይሰፍናል፤ በርካቶች የሕጉ ቅጣት እንዳያርፋባቸው ሲሉ መልካም ስብዕናን ተጎናጽፈዋል፤ ያጠፉት ስህተታቸው እንዳይደግሙት ተገስጸውበታል::

የኢሳ ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ በጅቡቲና በሶማሊያ ይኖራሉ:: በኢትዮጵያ በዋናነት ከሱማሌ ክልል 11 ዞኖች አንዱ በሆነው ሲቲ ዞን በስፋት የሚኖሩበት ነው:: ይህ ማለት ከድሬዳዋ ምዕራብ አቅጣጫ 90 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ሲቲ ዞን፣ በኢትዮጵያ የጅቡቲ ድንበር ላይ እስከ አዋሽ ድረስ እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ በስፋት ይኖራሉ::

ሔር ኢሴ በሦስቱም ሀገራት የሚኖሩ የኢሳ ማኅበረሰብ የሚተዳደሩበት ያልተጻፈ ሕግ ነው:: ሕጉ ሕዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስ እና ባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የማይዳሰሱ የባሕል ቅርሶች ጥበቃ የበይነ መንግስታት ኮሚቴ 19ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በማይዳሰሱ የሰው ልጅ ቅርሶች ወካይ ዝርዝር ውስጥ ተካቷል። ለኢትዮጵያ ስድስተኛው በዝርዝሩ የተካተተ የማይዳሰስ ቅርስም ነው::

በኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን የኢንታንጀብልና ኢትኖግራፊ ቅርስ ተመራማሪና የዲፓርትመንት አስተባባሪ ወይዘሮ ቀለሚ መኮንን ሕጉ በቅርስነት እንዲካተት መነሻ ጽሁፍ ከማዘጋጀት አንስቶ ሲመዘገብም ጉባኤው በተካሄደባት የፓራጓይ አሱንሲዮን ከተማ በአካል ተገኝታ የምስራቹን ሰምታለች:: እንደ አስተባባሪዋ ማብራሪያ፤‹‹ሔር ኢሴ›› በኢትዮጵያ በጅቡቲና በሱማሊያ የሚኖሩ የኢሳ ማኅበረሰብ አባላት በጋራ ሕጋችን ሲሉ የሚስማሙበትና የሚተዳደሩበት ሕግ ነው::

በተለያዩ ሀገራት የሚገኙት ኢሳዎች የሚጋሩት የመተዳደሪያ ሕጋቸውን ብቻ ሳይሆን መሪያቸውንም ነው:: መቀመጫው በድሬዳዋ ከተማ በሆነው ‹‹ኡጋዝ›› በጋራ ይመራሉ:: ኡጋዙ የሚሾመው መሪ ሲሆን፤ ለየት ያለ የጤና እክል ካልገጠመውና ማኅበረሰቡ አምኖበት የሾመውን ኃላፊነት እስከተወጣ ድረስ ሹመቱ የእድሜ ልክ ነው:: ግን ከማኅበረሰቡ ወግና ደንብ ያፈነገጠ ነገር ሲፈጽም ያኔ መሪነቱ ያበቃል:: ኢሳዎች ተሰብስበው በጋራ እንደሾሙት ተሰብስበው በጋራ ያወርዱታል:: ሕጉ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የወጣ ሲሆን፤ ሳይጻፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገረ ባሕላዊ ሕግ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል::

‹‹ሔር ኢሴ›› የኢሳ ማኅበረሰብ ያልተጻፈ ሕግ የማኅበረሰቡ መገለጫ እሴት ነው የምትለው ወይዘሮ ቀለሚ፤ ሔር ኢሴ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እየተላለፈና እየተተገበረ የመጣ መተዳደሪያ እንደሆነ ታስረዳለች:: አሁንም የሚተገበር የማኅበረሰቡ ሕያው ቅርስ እንደሆነም ትናገራለች:: ሕጉ የተጀመረው አሁንም በሀገራችን ማኅበረሰቡ በዋናነት በሚገኝበት ሲቲ ዞን በሚገኝ ሲቲ ተራራ ላይ እንደሆነም ታብራራለች::

እንደ አስተባባሪዋ ገላጻ፤ ከማኅበረሰቡ የተውጣጡ 44 አባቶች በብሔሩ አጠራር ‹‹ገንዴ›› የሚሰኙ በተራራው ላይ ክብ ሰርተው ወራትን ያስቆጠረ ምክክር አርገዋል:: በወቅቱ 44ቱን አባቶች ምግብ በማብሰልና አስፈላጊ ነገሮችን በማቅረብ ስታግዛቸው የነበረች ‹‹ሲቲ›› የምትባል ሴት ነበረች:: ተራራውና አካባቢው የእሷን ሥም ተጋርቶ መጠሪያው ሲቲ ሆኖ ቀረ::

እርስ በእርስ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት፣ ከቀላል እስከ ከባድ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ብሎም ሁሉንም እኩል የሚያስተዳድር ሕግ መደንገግ እንደሚያስፈልግ በማኅበረሰቡ አባላት በመታመኑ ባሕላዊ ሕጉ እንደወጣ ይነገራል። ሕጉ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ መሆኑና በሦስቱም ሀገራት የሚገኙ የኢሳ ማኅበረሰብ አባላት በአንድ መሪ መመራታቸው ልዩ ያደርገዋልም::

ወይዘሮ ቀለሚ እንደሚሉት፤ መሪው ሁሉንም እኩል ያገለግላል:: ሕጉ ለሴቶች፣ ለሕጻናት፣ ለአካባቢ ጥበቃና ለዘላቂ ሰላም ልዩ ትኩረት ይሰጣል:: የማኅበረሰቡ አባላት "ማንም ከሕጉ በላይ አይደለም፤ በታችም አይደለም፤ ሕጉ ለሁሉም እኩል ነው" የሚል አባባልም አላቸው:: በዚህም ሕጉን በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል ይጠቀሙበታል:: 160 አንቀጾች፣ 336 ንኡስ አንቀጾችና 444 መመሪያዎችም ያሉት ነው::

የነፍስ ግድያ ወይም የአካል ጉዳት የሚዳኝበት ክፍል ‹‹ሔር ዲግ›› ይሰኛል:: የንብረት ጉዳይ የሚታይበት ደግሞ ‹‹ሔር ደቀቃል›› ይባላል:: የሰብአዊነት መብት ጥሰት እንዳይኖር ጥበቃ የሚደረግበት የሕጉ ክፍል ‹‹ሔር ዴር›› በማለት ይጠሩታል:: የማኅበረሰቡ ባሕልና ወግ የሚጠበቀውን ሕግ ደግሞ ‹‹ሔር ደቃን›› ይሉታል:: የመሬት ጉዳዮች የሚታዩበት ‹‹ሔር ዲል››፤ በአካባቢው ለሚኖሩ ሌሎች ብሔረሰቦች ከለላ ማድረግን የተመለከቱ አንቀጾች ያሉበት ክፍል ‹‹ሔር ዲብለህ›› በመባል ይጠራሉ:: ከዚያም ባሻገር ማኅበረሰቡን የሚያስተዳድረው ኡጋዙ የሚመረጥበትና የሚሾምበት ሂደት በሕጉ የማኅበረሰቡን ባሕልና ወግ ለመጠበቅ በወጣው ሔር ደቃን በዝርዝር የተቀመጠበት ነው::

ሔር ኢሴ ከቀላል ጥፋቶች አንስቶ እስከ ከባድ ወንጀሎችን ይዳስሳል የምትለው ወይዘሮ ቀለሚ፤ ሕጉ በወረቀት አይጻፍ እንጂ በማኅበረሰቡ ልቦና ውስጥ ሰፍሯል::ኢሳዎች ለእያንዳንዱ ጥፋት ቅጣቱ ምን እንደሆነ ያውቁበታል:: ከቀላል አለመግባባት አንስቶ እስከ ግድያ የሚደርስ ጥፋት ሲከሰትም ይዳኙበታል:: ቅጣትም ያስተላልፉበታል ስትልም ታስረዳለች::

የጠፋው ጥፋት ቀላል በሚሆንበት ወቅት የፍትህ ሥራው የዛፍ ጥላ ሥር ይከናወናል:: ወንጀሉ ከፍ ያለ ሲሆንና የደም ካሳ የሚፈልግ ሲሆን ወንዝ መሃል ይካሄዳል:: በሕጉ ሴቶችና ሕጻናት የሚከበሩ ናቸው:: እነሱ ላይ መድፈር ጥቃትና ሌላም አላስፈላጊ ነገር ከደረሰ ፈጻሚው ይገለላል:: በእነዚህ ወንጀሎች ላይ ከበድ ያለና የማያዳግም ቅጣት ስለሚጣል በማኅበረሰቡ ዘንድ በብዛት እንደማያጋጥም ትናገራለች::

የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች እንደሚናገሩት፤ ሔር ለእነሱ ከምንም በላይ ነው:: ሁሉንም የሔር ኢሴ ባሕላዊ ሕግ አንቀጾች ያከብራሉ፤ ማሕበራዊ ችግሮቻቸውንም ይፈቱበታል:: ሔር ዲሞክራሲን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ፍትሐዊነቱ የጎላ ነው:: ምንም ይሆን ምን በኢሳ ማሕበረሰብ መካከል የተነሳ ችግርም ይሁን ግጭት ከሔር ኢሴ ውጭ አይሆንም:: ሕጉ ሁሉን አቀፍ በመሆኑ ማንኛውም የማሕበረሰቡን ወግና ባሕል የለቀቀ ነገር በሙሉ ይስተካከልበታል::

ኢሳዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ሕጉን እያጠኑት፤ ሲተገበር እያዩና እየተለማመዱ እንዲሄዱ ይደረጋል:: ሕጻንና ወረቀት የያዘውን አይለቅም ነውና ሔር ኢሴ በወረቀት ባይሰፍርም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ እዚህ ደርሷልም ይላሉ::

አስፈላጊ ሲሆን ኡጋዙ በተገኘበት በሦስቱም ሀገራት የሚገኙ የኢሳ ማኅበረሰብ ተወካዮች ተገናኝተው ይመክራሉ:: በዚህም ምን ክፍተት አለ? ምን ችግሮች አሉ? በቀጠናው ምን አጋጠመ? እንዴት ይፈቱ? በሚል ሳምንት የሚፈጅ መድረክ አላቸው:: ስለዚህም ሰዎች ሀገር አቋርጠው ይገናኛሉ፤ በቁምነገር ቀናት ወስደው ይመክራሉ::

ከዚህ ቀደም የማኅበረሰብ ተወካዮቹ በተገናኙበት አንድ ወቅት መታደም መቻሏን የምትናገረው አስተባባሪዋ፤ ኢትዮጵያና ጅቡቲ ድንበር አካባቢ በምትገኘው አይሻ በምትባል የሀገራችን ቦታ ተገናኝተው ሲመክሩ የተመለከተችበትን ሁኔታ እንደማትረሳው ትናገራለች:: በምክክራቸውም ጊዜ ወስደው መረጃ ተለዋውጠው ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ አስቀምጠው እንደሚለያዩ ምስክርነቷን ትሰጣለች::

የኢሳዎች የሕግ አከባበር ለሌሎች አካባቢዎችም የሚሆን ነው የምትለው ወይዘሮ ቀለሚ ሀገራትን ማስተሳሰሩ አንድ የሚለየው ነገር ነው:: መሪው (ኡጋዙ) ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ እንዲሁም ሶማሊያ ለሚገኙ የማኅበረሰቡ አባላት በእኩል የሚያገለግል መሆኑና ሕጉ በቃል ያለ መሆኑ የተለየ ባሕሪ ነው ባይም ናት::

ሀገራችን ከሔር ኢሴ በፊት አምስት የማይዳሰሱ ቅርሶችን አስመዝግባለች የምትለው አስተባባሪዋ ሔር ኢሴ ብዝኃ ሀገራዊ ሰነድ (መልቲናሽናል) የሚታይበት መሆኑ ልዩ እንደሚያደርገው ትገልጻለች:: ይህ ማለትም ከአንድ በላይ ሀገራት በጋራ ቅርሳቸውን ሲያስመዘግቡ የታየበት ነው በማለትም ታብራራለች::

በ2015 ዓ.ም ሕጉ በቅርስነት እንዲመዘገብ ለዩኔስኮ ሲቀርብ ኢትዮጵያ አስተባባሪ ነበረች:: ጅቡቲና ሶማሊያም ተሳታፊ ሆነው ሰነዱ ቀርቧል:: ሰነዱ ተዘጋጅቶ ከተላከ በኋላ ክትትል እንደሚያስፈልግ ስለታመነበት ኢትዮጵያ የአስተባባሪነት ሚናዋን ተጫውታለች:: ከሦስቱም ሀገራት ወኪል ቡድን ተቀምጦም ሥራውን እንዳከናወነ ታነሳለች::

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስ እና ባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የማይዳሰሱ የባሕል ቅርሶች ጥበቃ የበይነ መንግስታት ኮሚቴ 19ኛ መደበኛ ስብሰባውን በፓራጓይ አሱንሲዮን ባካሄደበት ወቅት በጉባኤው ላይ ተገኝተው ኢትዮጵያን በመወከል ንግግር ያደረጉት የሱማሌ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኢብራሂም ኡስማን፤ ዩኔስኮ ሔር ኢሴ የሶማሌ ኢሳ ማኅበረሰብን ያልተጻፈ ባሕላዊ ሕግ የሰው ልጆች ወካይ ዓለምአቀፍ የማይዳሰስ ቅርስ ሆኖ እንዲመዘገብ በማድረጉ ምስጋና አቅርበዋል::

ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ከኢዜአ ጋር በነበራቸው ቆይታም ሕጉ በዋናነት ችግሮች ሥር ሳይሰዱ እልባት በመስጠት የሚዳኝበት እና አሸናፊና ተሸናፊ ሳይኖር መፍትሔ በማበጀት ሰላምን ለማስፋን ያለው ፋይዳ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል። ባሕላዊ ሕጉ ሃይማኖት እና መደበኛ ሕግን የማይጻረርና ማኅበረሰቡ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ተስማምቶ ያጸደቀው መሆኑንም አመልክተዋል።

የረጅም ጊዜ የታሪክ እና የማንነት መገለጫ የሆነው ሕጉ በየዘመኑ ትውልዱ የራሱን አሻራ ያሳረፈበት ማኅበራዊ እሴት ነው:: ባሕላዊ ሕጉ መመዝገቡ ለሕጉ ቀጣይነት ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያደርግና የሦስቱን አገራት ማኅበረሰቦች በማስተባበር ሰላማቸው ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ እንዲጠበቅ ከማድረግ አኳያ ቁልፍ ሚና እንዳለውም አብራርተዋል። የሕጉ መጽደቅ ቀጣናዊ ትብብርን ለማጎልበት እና የተቀናጀ የቅርስ እንክብካቤና ጥበቃ ሥራ እንዲኖር አስተዋጽኦ እንደሚያደርግም አስረድተዋል።

እንደ አስተባባሪዋ ወይዘሮ ቀለሚ አስተያየት፤ ቅርሱ በመመዝገቡ ማኅበረሰቡ ይነቃቃል:: ባሕላዊ ሕጉ በዓለም መድረክ ሲነሳ ማኅበረሰቡ "ይሄም አለ" ብሎ ለባሕላዊ ውይይቶች እድል እንዲሰጥ ይሆናል:: ወጣቱ ስለቅርሱ እንዲያውቅና ትኩረት እንዲሰጥ ያግዛል:: ለቀጣይ ትውልድ ጠብቆ ለማስተላለፍ እድልም ይሰጣል:: ከአካባቢ ጥበቃ አንጻርም የመተግበሪያ ቦታዎች እውቅና እንዲኖራቸውና እንዲጠበቁ ያደርጋል:: የማኅበረሰቡን እሴትና ዋጋ ለመረዳት ያስችላል::

ቅርሱ የማኅበረሰቡ ቢሆንም ከተመዘገበ በኋላ የሀገር እንዲሁም የዓለም ጭምር ሆኗልና ለባሕል ትውውቅ፤ ለመከባበር፣ ለገጽታ ግንባታ፤ ባሕላዊና ማኅበራዊ ግንኙነትን ለማዳበር ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: ሌሎች ማኅበረሰቦች መሰል እሴታቸውን እንዲጠብቁና እንደሀገርም ትኩረት እንዲያገኝ እድል ይፈጥርላቸዋልም ብለዋል::

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ‹‹ባናርስ እናጣምዳለን›› ግብርናው በእርግጥም እየተለወጠ ነው!

ዘካርያስ

በሀገሪቱ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተከናወኑ የሚገኙ ልዩ ልዩ ተግባሮችን ተከትሎ በየዓመቱ የሚገኘው የምርት መጠን መጨመሩን ቀጥሏል:: መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ ከአንድ ዓመት በፊት የተገኘው ከ500 ሚሊየን ኩንታል የሚልቅ ዓመታዊ ምርት፣ ባለፈው ዓመት ወደ 700 ሚሊየን አካባቢ ከፍ ብሏል:: ዘንድሮ ደግሞ ይህ አሀዝ ከዚህ እንደሚልቅ ይጠበቃል::

ምርትና ምርታማነቱ ቀደም ሲል ይጨምር የነበረው የእርሻ መሬት በማስፋፋት ነበር:: ይህ አንድ መንገድ ነው:: በዚህ መንገድ በየዓመቱ በዘር የሚሸፈነው ማሳ መጠን ሲጨምር ቆይቷል፤ አሁንም እየጨመረ ነው፤ እንደሚጨምርም ይጠበቃል:: ሀገሪቱ ካላት ለእርሻ ሥራ ሊውል የሚችል መሬት አኳያ ሲታይ የተጠቀመችው ገና ውስኑን እንደመሆኑ በእርግጥም ገና ይጨምራል፤ እሰየው! ይጨምር!

ለግብርናው ምርትና ምርታማነት እየጨመረ መምጣት ሌላው መንገድ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ነው:: ከእነዚህ ቴክኖሎጂዎች መካከል አንዱ ማዳበሪያ ነው:: መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት ለማዳበሪያ አቅርቦት ለእዚያም በድጎማ ለማቅረቡ ሥራ ቅድሚያ እየሰጠ ሲሰራ ቆይቷል::

የውጭ ምንዛሪ እያለም በአንዳንድ ጫናዎች የተነሳ ማዳበሪያ ከውጪ ኩባንያዎች ማግኘት ፈተና በሆነበት ዓመት ማዳበሪያ ለመግዛት ያልወጣ ያልወረደበት ቦታ የለም:: ለማናቸውም በሚልም አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀም አጥብቆ እያሳሰበ ማዳበሪያውን እጁ እንደገባ ሲያቀርብ እንደነበርም ይታወሳል::

ማዳበሪያ ወደብ ከደረሰ በኋላም በአስቸኳይ አርሶ አደሩ ዘንድ እንዲደርስ ለማድረግ በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ በኩል የሚከናወኑ የተጠናከሩ ሥራዎች መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ማደግ ምን ያህል ዋጋ እየከፈለ እንደሚገኝ በሚገባ ያመላክታል::

የግብርና ምርምር ማዕከላት ያፈለቋቸው አዳዲስ ዝርያዎች /ቴክኖሎጂዎች/ ወይም የምርምር ውጤቶች ለግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት መጨመር የራሳቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: ማዕከላቱ በየዓመቱ ከሚያዘጋጃቸው የመስክ ጉብኝቶች መረዳት የተቻለውም ይህንኑ ነው፣ በእርግጥም ቴክኖሎጂዎቹ ለምርትና ምርታማነት መጨመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል::

ከምርምር ተቋማት የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች ለግብርና ምርትና ምርታማነት መጨመር ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ የዘርፉ ባለሙያዎች ብዙ የሚሉት ቢኖርም፣ በመስክ ጉብኝትና በመሳሰሉት የተገኙ መረጃዎች አስተዋጽኦአቸው ከፍተኛ ስለመሆኑ መናገር ያስችላሉ::

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ፣ አርሶ አደሩ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀም በመስራት በዘርፉ ለውጥ መምጣት ተችሏል:: በእነዚህ ቴክኖሎጂዎች አንዳንዶች ፈጥነው ተግብረው ተለውጠውባቸዋል፤ በዚያው ልክም አንዳንዶች ደግሞ በጥርጣሬ ሲመለከቱ፣ ቴክኖሎጂዎቹን ሲገፉ ቆይተው ሲቆጩም ተደምጧል:: እናም ከዚህ መቅረት ምን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል መገመት አይከብድም::

ይህ ሥራ በሔክታር የሚገኘው ምርት እየጨመረ እንዲመጣ፣ አዳዲስ የምርምር ውጤቶች በአርሶ አደሮች ማሳ እንዲሞከሩና ከዚህም ሌሎች አርሶ አደሮች ተሞክሮና ልምድ ቀስመው በቀጣዩ ዓመት ቴክኖሎጂዎቹን እንዲጠቀሙ ለማድረግ ተችሏል:: ተሞክሮዎቹን ይበልጥ ማስፋትና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ቴክኖሎጂዎቹ ውጤት ስለማምጣታቸው የአርሶ አደሮችን ማሳ አርሶ አደሮች እንዲሁም መገናኛ ብዙሃንና ግብርናውን የሚመሩ አካላት እንዲጎበኙ በማድረግ ለውጡን ለማስረዳት ተሰርቷል::

አርሶ አደሩ እያደር ቴክኖሎጂዎቹን ወደ መጠቀም እየገባ ባለበት ሁኔታ ምክንያቱ ምን ይሁን ምን በውል ባይታወቅም የምርጥ ዘር እንዲሁም የማዳበሪያ አቅርቦት መቆራረጥ ያጋጠመባቸው ወቅቶች እንዳሉ ይታወቃል:: ይህን ክፍተት ለመሙላትም ብዙ ተሰርቷል::

**አብዛኛው የሀገሪቱ የእርሻ መሬት አነስተኛ ማሳ ባላቸው አርሶ አደሮች እጅ ውስጥ እንደመሆኑ ይህን ደግሞ ሜካናይዝድ በሆነ መንገድ ለማልማት የግድ ኩታ ገጠም እርሻ እንደማስፈለጉ ኩታ ገጠም እርሻውን ለማስፋፋቱ ሥራ የበለጠ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል**

ማዳበሪያና ምርጥ ዘር መጠቀም የምርትና ምርታማነት ማሳደጊያ መንገዶች መሆናቸው ዛሬም ቀጥሏል፤ ነገም እንደዚያው ነው:: ለነገሩ ቴክኖሎጂ መጠቀሙ ተጀመረ እንጂ አይደለም እላይ ወገቡም አልደረሰ:: እነዚህ መንገዶች ምርትና ምርታማነቱን እያሳደጉት እዚህ ደርሰዋል:: ገና ምርትና ምርታማነቱን ይበልጥ ለማሻገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ሥራ ከገቡትና ውጤታማ ከሆኑት የስንዴ መስኖ ልማትና ኩታ ገጠም እርሻ እንዲሁም ሜካናይዜሽን ጋር በመሆን ታምር ይሰራሉ::

አሁን አሁን ደግሞ እነዚህ መንገዶች እንዳሉ ሆነው ለምርትና ምርታማነቱ እድገት አስተዋጽኦ በማበርከት በከፍተኛ ደረጃ እየተጠቀሱ ያሉት እነዚህ ኩታ ገጠም እርሻ፣ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፣ ሜካናይዜሽን የተባሉት የግብርናው ዘርፍ የእለት ተእለት አጀንዳዎች በእርግጥም በሀገሪቱ ግብርናውን ትራንስፎርም ለማድረግ ለተያዘው ርብርብ ትልቅ አቅም እየሆኑ ናቸው::

እንደሚታወቀው እነዚህን ሁሉ ርብርቦች ተከትሎ በሀገራችን የግብርና ምርትና ምርታማነት እያደገ መጥቷል:: ይህ ለውጥ ግን እስከ አሁንም እንደሚባለው ሀገሪቱ ካላት ለእርሻ አገልግሎት ሊውል የሚችል እምቅ አቅም፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪዎች ግብአት እንዲሁም ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ከሚያስፈልጋት የግብርና ምርት አኳያ ሲታይ የምርትና ምርታማነቱ እድገት ገና ውሃውም አልሞቀ የሚያሰኘው ነው:: ይሄ አምናም ካቻምናም ከዚያም ቀደም ሲልም ሲባል የቆየ ነው፤ ነገም ሊባል የሚችል ነው::

ይህ ማለት ግን በዘርፉ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተከናወኑ ሥራዎች የተገኙ ድሎችን ብድግ ብለን፤ ቆመን አናመሰግንም ማለት አይደለም:: በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተመዘገበው ታምር እንዴት ተደጋግሞ አይነሳ፣ እንዴት ተደጋግሞ አይደነቅ:: ይደነቃል፤ ገና ይደነቃል::

ከመረጃዎች መረዳት እንደተቻለው፤ የሀገሪቱ ዓመታዊ የስንዴ ምርት ግኝት ባለፈው ዓመት 250 ሚሊየን ኩንታል ደርሷል፤ መኸርም በልግም መስኖም ብሎ ማለት ነው:: ይህን አሀዝ ዘንድሮ 300 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል:: የተመጣበት መንገድም እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮችም ይህ እንደሚሳካ የሚያመላክቱ ናቸው::

በእዚህ ስኬት ውስጥ ደግሞ ከፍተኛውን ሚና እየተጫወተ ያለው በቅርቡ በዚህ የለውጥ ዘመን ወደ ሥራ የገባው የስንዴ መስኖ ልማት ያመጣው የምርትና ምርታማነት እድገት ነው:: ይህ ታምር ተደጋግሞ ሊደነቅ ይገባዋል:: ይህን ስኬት እኛ ብቻ ሳንሆን ፈረንጆቹም እያደነቁት ናቸው::

በዚህ ስንዴ ልማት ሀገር ዓመታዊ የስንዴ ፍላጎቷን ሸፍናለች፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ ለጎረቤት ሀገሮችም በመሸጥ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ችላለች:: በየዓመቱ ስንዴ ከውጭ ለመግዛት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ አስቀርታለች:: ስንዴ ከውጭ ለመግዛት ያለው ውጣ ውረድ፣ በስንዴው ጥራት ላይ የነበረው ጥርጣሬ፣

የሀገሪቱን የስንዴ ልማት ስኬት መንግስት ብቻ አይደለም ሁሌም በምርጥ ተሞክሮነት የሚጠቅሰው፤ የአፍሪካ ልማት ባንክ አንስቶ አይጠግብም፤ የታንዛኒያ ልኡካን ቡድን ሰሞኑን፣ቀደም ሲል የናይጀሪያ ልኡካን ቡድን ይህን ተሞክሮ ለመቅሰም ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል:: ፋኦ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጠው ሽልማት፣ ሀገሪቱ በቅርቡ ባስተናገደች ከረሃብ ነጻ ዓለም የመፍጠር ጉባኤ ሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ በአጠቃላይ በመስኖ ስንዴ ልማት ያሳየችው ለውጥ የተጠቀሰበት ሁኔታ የስንዴ ልማቱ በተለይ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ በአደባባይ የመሰከሩ ናቸው::

ሰፋፊ ለመስኖ እርሻ ሊውል የሚችል መሬት እንዲሁም ለመስኖ አገልግሎት ሊውል የሚችል ግድብና ወንዝ ባለው በቆላማው የሀገሪቱ አካባቢ አሀዱ ብሎ የጀመረው ይህ የስንዴ መስኖ ልማት ቆላ ደጋ ወይናደጋ ሳይል ተስፋፍቷል:: በየትኛውም ሥነምኅዳር ለመስፋፋት የሚያስችሉ ከበቂ በላይ ምቹ ሁኔታዎች የተፈጠሩለት ነውናም ገና ይስፋፋል::

ሀገሪቱ ምን ያህል ለሜካናይዜሽን እርሻ ባይተዋር ሆና እንደኖረች ይታወቃል:: የግብርና ባለሙያዎች ሁሌም ምክረሀሳብ ሲሰጡበት የቆዩት ይህ ቴክኖሎጂ አሁን እየተስፋፋ መጥቷል:: አርሶ አደሮች እየተደራጁም በግላቸውም ባለሀብቶች ኢንተርፕራይዝ እያቋቋሙም ትራክተሮችን ኮምባይነሮችን ወደ ገጠር እያስገቡ ናቸው:: መንግስትም በኢትዮጵያ ልማት ባንክ በኩል ለእዚህ ተግባር ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል::

በአንዳንድ የኩታ ገጠም እርሻ በተስፋፋባቸው አካባቢዎች በትራክተር ሲታረስና ማሳ በዘር ሲሸፈን፣ የደረሰው ሰብል በኮምባይነር ሲታጨድና ሲወቃ፣ ምርቱ በከባድ መኪኖች ወይም ማሳ ላይ በተዘጋጁ የምርት ማሳረፊያ ሥፍራዎች ላይ እንዲቆይ ሲደረግ መመልከት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመረው ጉዞ እምርታ እየታየበት ስለመሆኑ ለመመስከር ማሰብን አይጠይቅም::

ይህ ቴክኖሎጂ ከዓመት ዓመት እየጨመረ ነው:: ፍላጎቱም እንደዚሁ እየጨመረ ነው:: ምርትና ምርታማነቱም በእዚያው ልክ እንደሚጨምር ይጠበቃል:: የኩታ ገጠም እርሻም ከዓመት ዓመት መጨመሩን ቀጥሏል:: በደርግ ጊዜ ሰው በጣም ሲወፍር እንደመንግሥት እርሻ ሰፋህ ይባል ነበር:: አሁን ይህን አይነት ሰው ሲያጋጥም እንደ ኩታ ገጠም እርሻ ሰፋህ ሊባል ይችላል::

በቀጣይም መስፋፋት ይኖርበታል:: አብዛኛው የሀገሪቱ የእርሻ መሬት በአነስተኛ ማሳ ባላቸው አርሶ አደሮች እጅ ውስጥ እንደመሆኑ ይህን ደግሞ ሜካናይዝድ በሆነ መንገድ ለማልማት የግድ ኩታ ገጠም እርሻ እንደማስፈለጉ ኩታ ገጠም እርሻውን ለማስፋፋቱ ሥራ የበለጠ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል::

ግብርናው ለእርሻ አገልግሎት ሊውል የሚችል ሰፋፊ መሬት ወዳለበት ቆላማው አካባቢ እስከሚዘልቅ ድረስ ማድረግ የሚቻለውም ይህንኑ ነውና ኩታ ገጠም እርሻን ማስፋፋቱ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት በኩታ ገጠም እርሻ ሊታቀፍ የሚችል እጅግ በርካታ መሬት በአርሶ አደሮች እጅ ያለ እንደመሆኑም ኩታ ገጠም እርሻን ማስፋፋት ላይ በትኩት ሊሰራ ይገባል::

ግብርናው እየዘመነ ያለው በሰብል ልማት ብቻ አይደለም:: በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ዶ/ር በጉጂ ከጎበኙት ዘመናዊ የቡና እርሻ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው:: ይህ በሔክታር 60 ኩንታል ቡና ያስገኛል የተባለ የቡና ዘመናዊ ልማት በሔክታር የሚመረተውን ቡና ከ10 ኩንታል ወደ 60 ኩንታል የሚያሳድግ ነው::

ይህን እርሻ በቴሌቪዥን ተከታትለነዋል:: የሚመለከታቸው አካላት ይህን እርሻ ለምን እስከ አሁን እንዳላሳዩን ማብራሪያ ቢሰጡን መልካም ነው:: አንዳንድ ሰዎች አይተው ያምናሉ፤ ወደ ልማቱም ሊሳቡ ይችላሉ:: እነዚህ አይነቶቹ ሰዎች ይህን ልማት አይተው ልማቱን እንዲያስፋፉ ማድረግ ላይ መሰራት ነበረበት:: አሁንም አይረፍድም ተሞክሮው እንዲሰፋ ሊደረግ ይገባል::

በቅርቡ ሜድሮክ ኢትዮጵያ/ሆራይዘን ፕላንቴሽን/ ከአንድ የውጭ ኩባንያ ጋር ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችል ስምምነት መፈረሙ ይታወቃል:: ይህም በሔክታር በሚገኝ የቡና ምርታማነት ላይ ለውጥ ለማምጣት እንደሚያስችል ታምኖበታል:: ኩባንያው የቡናን ምርታማነት ለማሳደግ ያከናወናቸው ሥራዎችና የተገኘው ምርታማነት ብዙም ሳላላረካው ወደዚህኛው ልማት ለመግባት እንደወሰነ በወቅቱ የወጣ መረጃ ያመለክታል:: በልማቱ አብሮ ሊሰራ የገባው አንድ ታዋቂ የውጭ ኩባንያ እንደመሆኑ ከዚህም ብዙ እንጠብቃለን::

እናም ግብርናው መቀየሩን ቀጥሏል:: ለውጡን ለመመስከር የግድ የዘርፉ ባለሙያ መሆን አያስፈልግም፤ ኢኮኖሚዋ ግብርና በሆነ ሀገር ውስጥ መፈጠርና መኖር፣ ገጠሩን በትኩረት መከታተልና የመሳሰሉት ይበቃሉ፤ ለእዚህም ነው ‹‹ባናርስ እናጣምዳለን - በእርግጥም ግብርናው እየተለወጠ ነው›› ማለቴ::

በስንዴ መስኖ ልማት ላይ ብቻ አልተገደበም፤ በሩዝ፣ በለውዝ፣ በሻይ ልማት፣ ከፍ ብሎ እንደተመለከተውም በቡናውም ለውጥ ለማምጣት እየተሰራ ነው:: በሁሉም በተያዙት ርብርቦች ገና ብዙ ለውጥ እናያለን::


# ስፖርት





# በአትሌቶች ላይ የሚደርስ የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃት

**ቦጋለ አበበ**



ኦሊምፒክንና የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ከመሳሰሉ ታላላቅ የስፖርት መድረኮች በሚካሄዱበት ወቅት አትሌቶች ላይ የሚደርሱ የተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃቶች አሳሳቢ መሆናቸውን የዓለም አትሌቲክስ አሳውቋል። የዓለም አትሌቲክስ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ በሠራው የጥናት ግኝት መሠረት በአትሌቶች ላይ የሚደርሰው የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃት መጨመሩን አረጋግጧል። መሰል ጥልቅ ጥናት ሲደረግ በዓለም የስፖርት ማህበራት የመጀመሪያ እንደሆነም ተገልጿል።

አትሌቶች በትልልቅ የውድድር መድረኮች ሲያሸንፉ እንደሚደሰቱት ሁሉ ሽንፈት ሲገጥማቸውም ማዘናቸው አይቀርም:: የተመልካቹ ወይም የስፖርት ቤተሰቡም ስሜት ከዚህ የተለየ አይደለም:: የስፖርት ቤተሰቡ በሁለት መንገድ በማህበራዊ ሚዲያዎች አትሌቶች ላይ ጥቃት ያደርጋል:: ለምን አላሸነፈም ብሎ የገዛ ሀገሩ አትሌት ላይ ጥቃቱን የሚፈፅም አለ:: ‹‹የኔን ሀገር አትሌት ለምን አሸነፈ›› ብሎ ሌላው ላይ ጥቃት የሚሰነዝርም ብዙ ነው:: ጥቃቱ ዘር፣ የቆዳ ቀለምና ፆታን መሠረት ያደረገ ሲሆን ፆታዊ ትንኮሳንም ያካተተ ነው:: ይህም ትልልቅ የውድድር መድረኮችን ተከትሎ የሚመጣ ነው:: በዚህ መልኩ አትሌቶች ላይ የሚደርሰው የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃት በፓሪስ ኦሊምፒክ ወቅት ተባብሶ መታየቱን ጥናቱ አረጋግጧል::

ጥናቱ 2021 ላይ ከተካሄደው የቶኪዮ ኦሊምፒክ አንስቶ እስከ ፓሪሱ 2024 ኦሊምፒክ ድረስ ባለው ጊዜ በአትሌቶች ላይ የደረሱ የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ነው:: በዚህም ከትራክ (መም) እስከ የሜዳ ተግባራትና የጎዳና ላይ ውድድሮች የሚፎካከሩ የተለያዩ ሀገራት አትሌቶች በጥናቱ ተካተዋል:: እነዚህ አትሌቶች በቶኪዮና ፓሪስ ኦሊምፒኮች፣ በ2022 የኦሪገን፣ በ2023 የቡዳፔስት የዓለም ቻምፒዮናዎች የተሳተፉ 2438 መሆናቸው ተጠቁሟል::

በነዚህ ታላላቅ ውድድሮች ወቅት በአርባ ቋንቋዎች አትሌቶችን የተመለከቱ ከ1 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ የተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ልጥፎችና ግብረ መልሶች በጥናቱ ተተንትነዋል::

ጥናቱ በፓሪስ ኦሊምፒክ ወቅት የ1917 አትሌቶችና የስፖርቱ ሃላፊዎች የተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎችን እንደ ናሙና ወስዶ ክትትል አድርጓል:: ይህም በቶኪዮው ኦሊምፒክ ወቅት ከተወሰደው 161 ናሙና አስራ ሁለት እጥፍ የበለጠ ነው:: የቀድሞው ትዊተርና የአሁኑ X፣ ኢንስታግራም፣ ፌስቡክና ቲክቶክ ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው የማህበራዊ ሚዲያዎች ናቸው:: ጥናቱ በአትሌቶቹ የማህበራዊ ሚዲያዎች ገፅ ላይ የተሰጡ ግብረመልሶችን እንጂ በግል የተላኩ መልዕክቶችን አላካተተም::

በዚህም መሠረት ዘር ተኮርና ጾታዊ ትንኮሳን መሠረት በማድረግ አትሌቶች ላይ ያተኮሩ 48 በመቶ ጥቃቶች በፓሪስ ኦሊምፒክ ብቻ መመዝገባቸውን ጥናቱ ትኩረት ባደረገባቸው የማህበራዊ ሚዲያ ልጥፎችና ግብረመልሶች ታይቷል:: ከነዚህ ልጥፎች ውስጥም 809 ስድብ አዘል እንደሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን 128 ልጥፎችና አስተያየቶች (16 በመቶዎቹ) ተጨማሪ ምርመራ እየተደረገባቸው ነው:: በፓሪሱ ውድድር ወቅት ከ 1 ሺ 917 አትሌቶች ውስጥ ቢያንስ አንድ ንቁ የማበራዊ ድረ-ገጽ መለያ ያላቸው አትሌቶች፣ የስድብና እና ትንኮሳ ሰለባ መሆናቸውም ተጠቁሟል::

የዘረኝነት ጥቃቶች 18 በመቶና ፆታዊ ጥቃቶች 30 በመቶ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል። በዚህም መሠረት አጠቃላይ 20 የተለያዩ ሀገራትን በሚወክሉ አትሌቶች ላይ የተረጋገጠ ጥቃት ተፈጽሟል። 49 በመቶ በአሜሪካ አትሌቶች ላይ ነው::

ዘርና የቆዳ ቀለምን የተመለከቱ ጥቃቶች በወንድ አትሌቶች የከፋ መሆኑን የጠቆመው ጥናቱ ይህም በወንድ አትሌቶች ላይ ከሚደርሰው አጠቃላይ ጥቃት 26 በመቶ መሆኑን አስቀምጧል:: ሴት አትሌቶች በፆታዊ ጥቃትና በሌሎች ጉዳዮች ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸውም ታውቋል::

የዓለም አትሌቲክስ በአትሌቶች ላይ የሚደርሰውን ይህን የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃት ለማስቀረት ወደፊት ለሚወስዳቸው ርምጃዎች ጥናቱ ጠቃሚ ነው ተብሏል:: በአትሌቶች ደህንነት እና በአዕምሯዊ ጤና ዘርፍ ባለሙያዎች የሚሰጣቸውን ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ጨምሮ፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ የበለጠ ጠንካራ የድጋፍና ክትትል ሥርዓቶችን ለማዘጋጀትም ይረዳል ተብሏል።

የጥናቱን ግኝት ተከትሎ የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንት ሴባስቲያን ኮ ሲናገሩ፣ ‹‹ባለፉት አራት ዓመታት ይህን ጥናት ለማድረግ ብዙ ሀብት አፍስሰናል፣ በዚህም አትሌቶቻችንን ከመሰል የማህበራዊ ሚዲያ ጥቃቶች የምንከላከልበት መላ መዘየድ ቅድሚያ ሰጥተን የምንሠራበት ጉዳይ ይሆናል›› ብለዋል::